# የግልግል አመሠራረት ፥ ይዘትና ውጤት በኢትዮጵያ ሕግ

ከበዛወርቅ ሺመላሽ*

## መግቢያ

ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ በግለሰቦች መሀከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለሽማግሌዎች አቅርቦ በግልግል ለመፍታት የሚጠቀምበት የቆየ ልማዳዊ አሠራር ቢኖረውም፥[1] ከ1952 ዓ.ም. በኋላ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያገለግል ሰፊና ዘመናዊ የሆነ የግልግል ሥርዓት በሕግ መልክ ተቀርጾየወጣቢሆንም፥ የግልግል አሠራርን ትርጉምና ተግባራዊ አፈጻጸም አስመልክቶ ዛሬም ቢሆን በብዙ ወገኖች ዘንድ በቂ የሆነ ግንዛቤ የለም። የውጭ ተመራማሪዎችም ቢሆኑ ኢትዮጵያ ከቶውንም ግልግልን የሚመለከቱ ሕጎች የሏትም እስከማለት የደረሱባቸው ጊዜያቶችም አሉ።[2] አሁን ያሉት ሕግጋት የራሳቸው ጉልህ ችግሮች አሏቸው ከሚል ግምት በመነሳት አንዳንድ አካላት ዓለም አቀፍ የግልግል ጉዳዮችን በሚመለከት የየራሳቸውን ደንቦች ለማርቀቅ የሞከሩባቸው ጊዜያትም አይታጡም።[3] የድርጅት ሥራ አስኪያጆች ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ግልግልን የሚለከቱ ሕጎች መኖራቸውን በውል ለማወቅ ምንም ጥረት ሳያደርጉ ወይም እነዚህ የሕግ አናቅጽ የማይታለፉ ደንቦች መሆናቸውን ሳይገነዘቡ ፥ አለመግባባት ሲነሳ ጉዳዩ ፓሪስ በሚገኘው ዓለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት በኩል እንዲታይየሚያደርግ ስምምነት ውስጥ ሲገቡ ተዘውትሮ ይስተዋላሉ። የዚህ ጽሁፍ ዐበይት ትኩረትም ይህንኑ ችግር ለመዳሰስ ነው። ስለግልግል ሥርዓት ተግባራዊ አፈጻጸም ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች፥ የሕግ ባለሙያዎች፥ ነጋዴዎችና የድርጅት ሥራ አስኪያጆች አሁን በሥራ ላይ ካሉት የግልግል ደንቦች ጋር በመጠኑም ቢሆን እንዲተዋወቁለማድረግ ነው። የግልግል ፅንሠ ሀሳብ ሰፋ ያሉ ጉዳዮችን የሚያካትት ቢሆንም ይህ ጽሁፍ የግልግል ስምምነትን በሚመለከተው በአንደኛውገጽታ ላይ ብቻ ያተኩራል። በዚህም ስምምነቱ ምን ይመስላል፥ ስምምነቱ

---

* ኤል ኤል ቢ ፥ አዲስ አበባ ፥ ኤል ኤል ኤም ፥ ለንደን ፥ ኢንተርናሽናል የንግድ ሕግ አማካሪና ጠበቃ ፥ (ተርጓሚ ጥላሁን ተሾመ)።

1 ቶማስ ጌራሀቲ በኢትዮጵያ የበታችፍ/ቤቶች አሠራር ፥ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሄት ቅጽ 6 ቁጥር: 1(እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 1969) ገጽ 305፥

2 በማሰሩ ሌሴቶ እ.ኤ.አ. በሐምሌ ወር 1988 በተደረገው በኢንተርናሽናል ንግድ ህግ አህጉራዊ ሴሚናር ላይ በ "ፒቲኤ አባል አገሮች ስላለው የግልግል ዳኝነት ህጎች" በማለት የቀረበውን ፅሁፍ ይመልከቱ።

3 የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት እ.ኤ.አ. በ1988 ዓ.ም. ያወጣውን የኢንተርናሽናል ንግድ ግልግል ዳኝነት ተብሎ የተዘጋጀውን ረቂቅ አዋጅ ይመልከቱ።

ግልግል

እንዴት ይከናወናል፥ የስምምነቱ ይዘትና ሕጋዊ ውጤት ምንድነው፥ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሙከራ ይደረጋል። በተጨማሪም ከዓለም አቀፍ የግልግል ደንብ ውስጥ የተያዘውን ጉዳይ የሚመለከተውን አንድ ክፍል እዚሁ ውስጥ ማግባት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ እንዲታወቅ የሚፈለገው ይህ ጽሁፍ ተዋዋይ ወገኖች በራሳቸው ፍላጎት የሚመሠርቱትን የግልግል ስምምነት ብቻ የሚመለከት መሆኑ ነው። በሕግ አስገዳጅነት የሚደረጉ የግልግል ሥርዓቶችን አይዳስስም። በመሆኑም የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኝነት ፥ የአሠሪና ሠራተኛ የግልግል ዳኝነትና ቀደም ሲል ማዕከላዊ አስታራቂ ኮሚቴ እየተባለ ይጠራ ለነበረው አካል ይቀርቡ የነበሩ የግልግል ጉዳዮች ከዚህ ጽሁፍ የትኩረት አድማስ ውጭ ናቸው።

## ክፍል አንድ

## የግልግል ስምምነት አመሠራረት

### ሀ. የግልግል ስምምነት ትርጉምና ባህርይ

እንደአንድ የክርክር መቋረጫ ዘዴ ግልግል የሚመሠረተው በተገላጋዮች የጋራ ስምምነት ሲሆን ይህም የግልግል ስምምነት በመባል ይታወቃል። የግልግል ስምምነት የሚለው ሐረግ በፍትሐ ብሄር ሕጉም ሆነ በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንድ ወጥ በሆነ አኳኋን እጥቅም ላይ የዋለ አነጋገር ነው። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ግን የግልግል ስምምነትና የግልግል ውል የሚሉትን አገላለጾች እንደአገባቡ በማለዋወጥ ለመጠቀም ሙከራ ይደረጋል። ምክንያቱም የአማርኛውም ሆነ የእንግሊዝኛው የፍትሐ ብሄሩ ሕግ ቅጅ የተተረጎሙት ሕጉ ከተረቀቀበት ከዋናው የፈረንሣይኛው ረቂቅ በመሆኑና ይህም ዋና ረቂቅ "la convention d'arbitrage" በሚለው አነጋገር ፅንሠ ሀሳቡን ስለሚገልጸው ነው።[4]

" በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ ስለሚደረግ ስምምነት " የሚለው አባባልም አልፎ አልፎ በፍትሐ ብሄር ሕግ እና በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ ፥ ሠፍሮ ይገኛል።[5] ይህም ያው የግልግል ስምምነት ማለት ነው።[6] ልዩነቱ በዚህኛው አነጋገር ስምምነቱ ራሱን ችሎ በቆመ ውል የተደረገ አለመሆኑና መጀመርያውኑ ዋናው ውል ሲደረግ እንደ አንድ የውል አንቀጽ ሆኖ እንዲሠፍር አመደረጉ ላይ ነው።

---

[4] ሀራፕ የኪስ የፈረንሳይኛና የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ይመልከቱ።

[5] የፍትሐ ብሄር ህግ ቁጥር 3328 (ርዕስ ይመልከቱ)፥ ከዚህ በኋላ ፍ.ሕ. ተብሎ የሚመለከት፥ የባህር ህግ ቁጥር 209፥

[6] አሰፋ ደስ ፥ <u>በኮንስትራክሽን ውሎች ስለሚደረግ የግልግል ዳኝነት</u> ፥ ለህግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቀን ያልተጻፈበት የመመረቅያ ጽሁፍ ፥ ገጽ 8 ፥ (በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ)፥

የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3325(1) ግልግል የሚለውን ቃል እንደሚከተለው ይተረጉመዋል። "ተዋዋይ ወገኖች የአንድ ክርክርን ውሳኔ ለአንድ የዘመድ ዳኛ ለሆነው ለአንድ ሦስተኛ ሰው አቅርበው የዘመድ ዳኛው ውል በሕግ አግባብ መሠረት ይህንኑ ክርክር ለመቁረጥ የሚያደርገው ውል ነው።" ለዘመድ ዳኛው የሚቀርቡት የፍሬ ነገር ክርክሮች ብቻ እንደሆኑና[7] የገላጋዮቹም ቁጥር አንድና ከዝያም በላይ ሊሆን እንደሚችል በተጨማሪ ተመልክቷል።[8] የግልግል ስምምነት ውል እንደመሆኑ መጠን በመጀመርያ ግልግልን በሚመለከቱት የሕጉ ልዩ ደንቦች ፣ ከዝያ ካለፈ ደግሞ በፍትሐ ብሄር ሕግ አራተኛ መጽሐፍ፣ አንቀጽ 12 ውስጥ በሚገኙት አጠቃላይ የውል ደንቦች መሠረት የሚመራ ነው።[9]

ምንም እንኳ የግልግል ስምምነት ውል ነው ቢባልም በተለያዩ መልኮች የራሱ መለያ ባህርያት የሚታዩበት ነው። ከእነዚህ አንዱን ባህርይ ሎርድ ማክሚላን እጥር ምጥን አድርገው ሲያስቀምጡ እንዲህ ብለውታል።

> "... ሌሎች የውል ኃይለ ቃላት የተዋዋይ ወገኖችን ተነፃፃሪ ግዴታዎች የሚያስቀምጡ ናቸው። ግልግልን የሚመለከቱት ኃይለ ቃላት ግን ተዋዋይ ወገኖች አንዱ ለሌላው የሚገቡበትን ግዴታ የሚያመለክቱን አይደሉም። እነዚህ ኃይለ ቃላት የተዋዋዮችንግዴታ በተመለከተ በመሀከላቸው ክርክር በሚነሳበት ጊዜ ክርክሩ ራሳቸው ተዋዋዮችባቋቋሙት የዳኝነት ሰሚ አካል እንዲታይና እንዲወሰንየሚያደርጉትን ተጨማሪ ስምምነት የሚያመለክቱን ናቸው።"[10]

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በግልግል ስምምነት (ወይም ስለግልግል በተቀመጡ የውል ኃይለ ቃላት) ተዋዋዮቹ የሚያቋቁሙት ግዴታ አንደኛው ከሌላው የሚጠይቀው ወይም አንደኛው ለሌላው የሚፈጽመው ሳይሆን ውላቸውን አስመልክቶ በመሀከላቸው ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ በገላጋይ እንዲታይ የሚደረግበትን አኳኋን ነው።

በሬኔ ዴቪድ አባባል እንደተገለጸው ሌላው የግልግል ስምምነት ገጽታ ደግሞ "በአንድ በኩል ተዋዋዮቹ ጉዳያቸውን ለገላጋዩ ለማቅረብ የፈቀዱበት አንድ ስምምነት እና በሌላ በኩልም በተዋዋዮቹና በገላጋዩ መሀከል ለመሸምገል የተደረገ ሌላ ስምምነት በአንድ ጉዳይ ላይ ተዋሀዶ" መገኘት ነው።[11] ይህ የሁለት ስምምነቶች ውህደት "የዘመድ ዳኛው ውል በሕግ አግባብ መሠረት ይህንኑ ክርክር ለመቁረጥ የሚያደርገው ውል ነው" ተብሎ ስለግልግል ትርጉም

---

[7] ቁጥር 3325(2) ፍ.ሕ.

[8] ቁጥር 3331(2) ፍ.ሕ.

[9] ቁጥር 1676(1) እና (2) ፍ.ሕ.

[10] <u>በግልግል ዳኝነት ህግ ኢንሳይክሎፒዲያ</u>፣ ሄይሚንና ሎላ ከዳርዊንስ ሊሚትድ ጋር ስለቀረበው ክርክር ኤሪክሲ በፃፉት ፅሁፍ በሎይድስ ኦፍ ለንደን ፕሬስ እ.ኤ.አ. በ1984 የተፃፈውን ክፍል 3.1.3. ይመልከቱ።

[11] ሬኔ ዴቪድ ፣ <u>በኢንተርናሽናል ንግድ የግልግል ዳኝነት</u> በማለት የፃፉት መፅሐፍ ፣ ክሉዌር አሳታሚዎች ፣ ዴቬንተር ፣ ኔዘርላንድስ ፣ እ.ኤ.አ. 1985 የታተመ ፣ ገጽ 78፣

በተሠጠበት የፍትሐ ብሄር ሕጉ አንቀጽ በግልጽም አኳኋን ተቀምጧል። የግልግል አሠራር ገላጋይ በመሾም ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የተሾመው ገላጋይ ጉዳዩን ለማየት ፍቃደኛ መሆኑንም እንዲያረጋግጥ ይገባል። ለዚህም ነው በሕጉ ላይ "ለዘመድ ዳኝነት የተመረጠው ሰው ይህንን ሥራ ለመቀበል ወይም ላመቀበል ነፃ ነው"[12] ተብሎ የተገለጸው። በተዋዋዮቹ እና በገላጋዩ መሀል የሚደረገው ሁለተኛው ስምምነት ፣በማለት ዴቪድ የሠነዘሩት ሀሳብ ውጤት የሚኖረውም ገላጋዩ ይህን ሀላፊነት መቀበሉን ከገለጸ በኋላ ነው።

አሁንም ሌላው የግልግል ስምምነት ልዩ ባህርይ ተከራካሪ ወገኖች በመሀከላቸው የሚፈጠረውን አለመግባባት ተቀብሎ ለማየት የሚችል የራሳቸው የሆነ የዳኝነት አሠራር ለመፍጠር የመቻላቸው ሁኔታ ነው።በዚህ አሠራር ተከራካሪዎች ራሳቸው በግል የሚመርጧቸው ዳኞች ይኖሯቸዋል ማለት ነው። ሁለቱም ክርክራቸውን እስከወድያኛው ለማዝለቅ ከተሰማው የመደበኛ ፍርድ ቤቶችም ሆነ የመንግሥት አካላት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ ሳይሆን ለክርክራቸው የመጨረሻ ዕልባት ለመስጠት ይቻላቸዋል ማለትም ነው።

## ለ. የግልግል ውል አመሠራረት

የግልግል ውል እንዴት ይመሠረታል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስለውሎች በጠቅላላው በፍትሐ ብሄር ሕግ ከቁጥር 1678-1730 የተመለከቱትን ደንቦች መመልከት ያስፈልጋል። ይህን አይነት ውል የሚመሠረተው አንደኛው ወገን ስለዚሁ ስለግልግል ጉዳይ የሚያቀርበውን የውለታ ሀሳብ ሌላኛው ወገን ያለምንም ቅሬታ ሲቀበለው ነው። ይህ የውል አቀራረብና የውል አቀባበል "በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሣ ግዴታ ለመግባት መፍቀዱን በማያጠራጥር አሠራር በማስታወቅ" ይገለጻል።[13]

በኢትዮጵያ አስመጭና ላኪ ኮርፖሬሽን (ኢትሜክስ) እና ቢ.ቪ.ቬረኒጊዴ አሊየፋብሪይክን (አይሎስ) እየተባለ በሚጠራው የደች የምግብ ዘይት አከፋፋይ ድርጅት መሀከል ተደርጎ የነበረው ድርድር የተያዘውን ጉዳይ በተመለከተ በዓይነተኛነት የሚጠቀስ ምሳሌ ነው።[14] በኢትሜክስ በተዘጋጀውየጨረታ ሰነድ የሚፈለገው ዕቃ ዓይነትና ብዛት ከተገለጸና ሌሎችም የውለታ ሁኔታዎች ከተመለከቱ በኋላ የውጭ ሀገርኛ አቅራቢዎች ለቀረበው ጨረታ ምላሽ ይሠጡ እንደሆን በቴሌክስ ጥሪ ተላለፈላቸው። በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የዚህ አይነት አሠራር ሀሳብን እንደመግለጽ እንጂ እንደውል አቀራረብ ተደርጎ አይወሰድም።[15] እንደአንድ የጨረታ ተወዳዳሪ በመሆን አይሎስ

---

[12] ቁጥር 3339(3) ፍ.ሕ.

[13] ቁጥር 1681(1) ፍ.ሕ. ስለ ስምምነቱ (ፎርም) በተለየ ርእስ እንወያይበታለን።

[14] የኢትሜክስ የህግ ክፍል መዝገብ፣ አይሎስ በተባለው ድርጅት ላይ በሮተርዳም ከተማ ውል በማፍረስ ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ለኢትሜክስ ድርጅት ወስኖለታል።

[15] ቁጥር 1687(1) ፍ.ሕ.

የተባለው ድርጅት ለተደረገው ጥሪ የራሱን የውል አቀራረብ በቴሌክስ አስተላለፈ። ይህ የውል አቀራረብ በኢትሜክስ ተቀባይነት በማግኘቱ በሁለቱ ወገኖች መሀከል የሽያጭ ውል ተደረገ። ይህ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ስለግልግል የተወሰነ ምንም ነገር አልነበረም። ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢትሜክስ የክሬዲት ሰነድ (ሌተር ኦፍ ክሬዲት) በባንክ በኩል ለመክፈት ያስችለው ዘንድ አይሎስ የዕቃ አቅርቦት የውሉን ረቂቅ እንዲልክለት ጥያቄ አቀረበለት። በዚህ ጥያቄ መሠረት አይሎስ የሚከተለው አንጋገር ያለበትን የውል ረቂቅ ላከለት።

> ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ውል ምክንያት ወይም ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚነሱትን ክርክሮች ሁሉ ኢን.አ.ኢፍ.ኢ.ቲ.ኢ. እየተባለ በሚታወቀው የግልግል ደንብ መሠረት እንዲታይላቸው ሮተርዳም ለሚገኘው የግልግል ተመልካች አካል ለማቅረብ እነሆ ተስማምተዋል።[16]

ኢትሜክስ በበኩሉ ይህን ስለግልግል የተደረገውን የውል አቀራረብ ከተመለከተ በኋላ ስለግልግል የሠፈረውን የውል ኃይለ ቃል ተጥሎ ባለው አኳኋን በማሻሻል ምላሹን ሠጠ። "<u>ስለግልግል</u> ፤ በዚህ ውል ምክንያት ወይም ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚነሳ ማናቸውም ክርክር ሁሉ ፓሪስ ለሚገኘው አይ.ሲ.ሲ.[17] ለተባለው አካል እየቀረበ በግልግል ይታያል።"

የኢትሜክስ ምላሽ ስለግልግል በመጀመርያ ከተሠጠው የውል አቀራረብ ጋር የሚጣጣም ስላልሆነ በራሱ ግልግልን የሚመለከት አዲስ የውል አቀራረብ እንደሆነ ተደርጎ ነበር የተወሰደው።[18] ይህ አዲስ የውል አቀራረብ በአይሎስ ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ አንድ የግልግል ውል በሁለቱ መሀከል ተደርጓል ማለት እንችል ነበር። ክፋቱ ግን ይህ ከመሆኑ በፊት በሁለቱ ወገኖች መሀል ውዝግብ በመከሰቱ ግልግልን በተመለከተ ምንም ዓይነት ውል ሳይደረግ መቅረቱ ነው። ይህ ጉዳይ የግልግል ስምምነት የሚመሠረትበትንና የሚከናወንበትን ሁኔታ እንደዚሁም በግልግል ስምምነትና በዋናው ውል መሀል ያለውን ልዩነት ደህና አድርጎ ያሳየናል።[19]

## ሐ. <u>ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ውልን ለማድረግ ስላላቸው ችሎታ</u>

ምንም እንኳ የሰዎችን ችሎታ የሚመለከቱ ደንቦችን በሥነ ሥርዓት ሕጎች ደንግጎ ማስቀመጥ የሚቻል ባይሆንም የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን ስለዚሁ ጉዳይ " ማንም ሰው

---

16 "ኔዘርላንድስ አይልስ ፋትስ ኤንድ አይል ሲድስ ትሬድ አሶሴሽን" እየተባለ የሚታወቀው አካል የወጣው የግልግል ደንብ ነው።

17 "ኢንተርናሽናል የንግድ ምክር ቤት"

18 ቁጥር 1694 ፍ.ሕ.

19 "ድርድር እና የግልግል ስምምነት ማስረጃ አቀራረብ" በሚል ንዑስ ርዕስ ሥር ዝቅ ብሎ የሠፈረውን አስተያየት ይመልከቱ።

ጉዳዩን በግልግል ለማስወሰን ችሎታ ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ክርክሩን በግልግል ዳኝነት ለማስወሰን አይችልም "ሲል ይገልጻል።[20] እላይ እንደተገለጸው እዚህም ላይ ቢሆን ሕጉ "ችሎታ ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር" የሚለውን ሐረግ በመጠቀም የችሎታ ጉዳይ በሌሎች መሠረታዊ ሕጎች የሚደነገግ መሆኑን ነው የሚያስገነዝበን። በመሆኑም በግልግል ዳኝነት ክርክሮች እንዲታዩ ለማድረግ የሚኖርን ችሎታ አስመልክቶ የፍትሐ ብሄር ሕጉ እንዲህ ይላል። "መብትን ያለዋጋ ለመስጠት ስለመቻል የሚያስፈልገው ችሎታ በዚሁ መብት የተነሳውን ክርክር በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ ለሚደረገውም ውል አስፈላጊ ነው።"[21]

የግልግል ስምምነቱ ተዋዋይ የተፈጥሮ ሰው የሆነ እንደሆነ ከሁሉም አይነት የችሎታ ማጣት እንከኖች የጸዳ መሆን ያስፈልገዋል። ይህ አከራካሪ ነገር አይደለም።[22] ተዋዋዩ ወገን የተፈጥሮ ሰው ያልሆነ እንደሆነ ደግሞ ሕጋዊ ሰውነትን የተላበሰ እንዲሆን ያስፈልጋል። ይህም የማያከራክር ነው።እልቅየስ እዚህ ላይ ትኩረት ልንሠጥ የሚገባን "መብትን ያለዋጋ ለመስጠት ስለመቻል የሚያስፈልገው ችሎታ" በሚለው ሐረግ ስለተገለጸው ተጨማሪ መለከያ ነው።

የግልግል ውሎች ከመደበኛዎቹ ውሎች በባህርያቸው የተለዩ መሆናቸውን ከፍ ብለን አመልክተናል። እነዚህ ውሎች ተዋዋዮቹ ለየት ባለና ግላዊ (መንግሥታዊ ባልሆነ) በሆነ የዳኝነት ስሚ አካል አለመግባባቶቻቸው እንዲታዩ የሚያደርጉትን ስምምነቶች የሚመለከቱ ናቸው። ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊያገኙ ከሚችሉት ውሳኔዎች የተለዩ ውሳኔዎች ሊሠጡ ወደሚችሉባቸው አሠራር ሊያመሩ የሚችሉም ናቸው።[23] ስለሆነም በሕጉ የአማርኛው ቅጅ " ያለዋጋ " ተብሎ እንደተቀመጠው ተዋዋዮቹ ነገሩን አመች ሆኖ ባገኙት መንገድ ለመጨረስ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑ አስፈላጊ ይሆናል። ተዋዋይ ወገኖች ውሉን የሚያደርጉት በራሳቸው የግል ችሎታ ሳይሆን በሌሎች የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰዎች ስም የሆነ እንደሆነ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ እንዲስማሙ የሚያስችላቸው ልዩ የውክልና ሥልጣን እንዲኖራቸው ይገባል።[24] የዚህ ዓይነቱን ሥልጣን የሚሠጠው ደግሞ ራሱ የሕግ ችሎታ ያለው ዋናው ወካይ ነው። ወካዩ እንደ የንግድ ማህበር ያለ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ አካል በሚሆንበት ጊዜ ይህን ሥልጣን የሚሠጠው የማህበሩ የበላይ አመራር ነው። የዲሬክተሮች ቦርድ በዚህ ረገድ ለአብነት ሊጠቀስ ይችላል።[25]

---

20 ቁጥር 315(3) የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከዚህ ቀጥሎ "ፍ.ሕ.ሥ.ስ."

21 ቁጥር 3326(1) ፍ.ሕ.

22 ቁጥር 1678(ሀ) ቁጥር 192-194 ፍ.ሕ. እነዚህ የችሎታ አለመኖር ሁኔታዎች ካሉ በሞግዚቱ አማካኝነት ተግባሮቹ ይከናወናሉ። ቁጥር3327(2) ፍ.ሕ.

23 ከላይ በተራ ቁጥር 11 በተጠቀሰው የግርጌ ማስታወሻ የተገለጸው የዳኺድ ፅሁፍ ገፅ 174

24 ቁጥር 2205 ፍ.ሕ.

25 ቁጥር 313(10)፥ 347(2)፥ 363(1) የንግድ ሕግ

ስለተፈጥሮ ሰዎችና ስለንግድ ማህበራት ችሎታ ይህን ያህል ካልን በቂ ይመስለናል። በዚህ ረገድ ብዙውን ጊዜ አወዛጋቢ ጥያቄዎች የሚነሱት ይህ የችሎታ ጉዳይ መንግሥትን፣ የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶችንና የመንግሥት የልማት አውታሮችንበሚመለከትበት ወቅት ነው። ይህም የሚሆነው እነዚህ አካላት የሚያከናውኑት ተግባር የሕዝብን ጥቅም የሚነካ ስለሚሆን ነው። ጥያቄው ታድያ ቀጥሎ ያለው ይሆናል። እነዚህ አካላት የግልግል ውልን ለማድረግ ችሎታው አላቸውን? አላቸው ከተባለ የችሎታቸው አድማስ እምን ድረስ ይዘልቃል?[26]

እስቲ ከሁሉም በፊት ራሱን የኢትዮጵያን መንግስት እንውሰድ። የፍትሐ ብሄር ሕጉ "መንግስት በሕግ በኩል እንደአንድ ሰው የሚቆጠር ነው " ብሎ ይገልጽና " እንዲህ እንደመሆኑ መንግሥት በመሥርያቤቶቹ አማካይነት ከተፈጥሮው ጋር የሚስማሙትን መብቶች ሁሉ ሊያገኝና ሊሠራባቸው ይችላል " ብሎ ያብራራዋል።[27] በመንግሥትና በመስተዳድሩ መሀል ባለው የንድፈ ሀሳብ ልዩነት ብዙም ሳናተኩር ለምሳሌም ያህል የኢትዮጵያ መንግሥት የነዳጅ ዘይት ውልን አስመልክቶ ሊነሳ የሚችልን ክርክር በግልግል ለመጨረስ የሚያስችል መብት በሕግ ተሠጥቶታል።[28] እንደዚሁም መንግሥት የጋራ ልማትን በተመለከተ በተደረገ ውል ተዋዋይ ሆና በሚገኝበት ጊዜ በውሉ የተነሳ የሚመጣውን ክርክር በግልግል ለመጨረስ የሚያስችል መብት አለው።[29] ከእነዚህ ሌላ መንግሥት የገልግል ስምምነትን ለመደራደር መብት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን በመግለጽ የሚናገር አጠቃላይ ደንብ አላገኘንም። ከዚህ በመነሳት መንግሥት የግልግል ስምምነትን ለማድረግ የሚያበቃ ችሎታ የለውም ብሎ በቀላሉ መደምደም አያዳግትም ነበር። ነገር ግን ይህ ከገሀዱ እውነታ ጋር የሚጣጣም አይደለም። ችሎታን የሚመለከቱትን ደንቦች ጨምሮ መንግሥት የሁሉም ዓይነት መብትና ግዴታዎች እንደዚሁም ሕጎች ምንጭ ነው። የሕዝብ ንብረት ባለአደራም ነው። ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳትም ለግልግል የሚቀርበው መብት የመንግሥት እስከሆነ ድረስ ፣ ማለትም የሌላ አካል የግለሰቦችና የቡድኖች እስካልሆነ ድረስ፣ መንግሥት የግልግል ውሎችን የማድረግ ችሎታ አለው ብሎ መናገር ይቻላል።

የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶችንና የመንግሥት የልማት አውታሮችንበተመለከተ በርከት ያሉ አዋጆችን ጠቅለል ባለ መልክ ከዳሰስን በኋላ በሦስት ምድቦች አስቀምጠናቸዋል። እነዚህም የግልግልን ስምምነት ለማድረግ ግልፅ መብት የማይሠጡ ፣ የተገደበ መብት የሚሠጡና ግልፅ መብት የሚሠጡት ናቸው።

---

26 በግልግል ዳኝነት ሊፈቱ የሚችሉ እና ሊፈቱ የማይችሉ አለመግባባቶችን በተመለከተ ዝቅ ብሎ ማብራሪያ ይሰጥበታል።

27 ቁጥር 394 ፍ.ሕ.

28 የፔትሮሊየም ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 295/1979 ቁጥር 25

29 የጋራ ልማት ማህበር የመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 11/1982 አንቀጽ 4(1) እና አንቀጽ 36

እንደኢትዮጵያ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን [30] ያሉት የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶች ውልን ለመዋዋል፥ ለመክሰስና ለመከሰስ፥ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ለመስጠት የሚያስችል ሥልጣን ተሠጥቷቸዋል። ክርክራቸውን በግልግል ለመጨረስ እንዲስማሙ የሚያደርግ ሥልጣን ግን በግልፅ አልተሠጣቸውም። ይህ ሁኔታ እንደ ኢትዮጵያ የእርሻ መሣርያዎች አቅራቢ ኮርፖሬሽን ያሉትን የመንግሥት የልማት አውታሮችንም ይመለከታል።[31] በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ማከፋፈያ ኮርፖሬሽንና[32] እንደ ኢትዮጵያ አስመጭና ላኪ ኮርፖሬሽን[33] ያሉትን የመንግሥት የልማት አውታሮች የተመለከትን እንደሆነ በተቆጣጠረው የሚኒስቴር መሥርያ ቤት ፈቃድ ክርክሮችን ከፍርድ ቤት ውጭ ለመጨረስ የሚያስችላቸው መብት አላቸው። ይህም መብት ገልገልን እንደሚጨምር ይገመታል። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ እንደ የአየር ትራንስፖርት ባለሥልጣን[34] ወይም እንደ ብሄራዊ የውሀ ሀብት ልማት ኮሚሽን[35] ያሉ ብዙ የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶች ክርክርን በግልግል ለመጨረስ የሚያስችል ግልጽ የሆነ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። እንደ ጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን[36] ዓይነቶቹ የመንግሥት የልማት አውታሮችም ተመሳሳይ ሥልጣን አላቸው። ከዚህ ግንዛቤ የሚደረስበት መደምደምያ የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶችንና የመንግሥት የልማት አውታሮችን በተመለከተ ለግልግል የመቅረብ ችሎታ በጥቅል የሚታይ አለመሆኑ ነው። እነዚህ አካላት አንድም በሕግ የተመለከተ ግልጽ ሥልጣን እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። አልያም የልማት አውታሮች ከሆኑ ይህን ለማከናወን የሚያስችላቸው ልዩ ፈቃድ እንዲኖራቸው ግድ ይሆናል።

መ. <u>የግልግል ስምምነት አቀራረጽና የግስረጃ አቀራረብ ሥርዓት፥</u>

የውሉ አቀራረጽ (ፎርም) ጉዳይ የግልግል ውል መደረግ ያለበት በቃል ነው ወይስ በጽሁፍ ለሚለው ጥያቄ ከሚሠጠው ምላሽ ጋር የተያየዘ ነው። በዚህ ረገድ ይህን ጉዳይ የሚገዛው የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3326 (2) እንዲህ ይላል:-

---

30 አዋጅ ቁጥር62/1968

31 አዋጅ ቁጥር269/1977

32 የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 104/1980 አንቀጽ 12 (3)

33 የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ደንብ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 14/1968 እና ቁ. 5/1968 አንቀጽ 7 (2)

34 አዋጅ ቁጥር 111/1970 ቁጥር 8 (18)

35 አዋጅ ቁጥር 217/1974 ቁጥር 8 (16)

36 አዋጅ ቁጥር 234/1974 ቁጥር 10 (2) (ሐ)

"በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ የሚደረገው ስምምነት በሕግ ይሆንኑ መብት ያለዋጋ ለመስጠት አስፈላጊ በሆነው ፎርም ዓይነት መፈጸም አለበት።"

በዚህ አስቸጋሪ በሆነ አንቀጽ መንፈስ የሄድን እንደሆነ መብትን ያለዋጋ መስጠትን የሚመለከቱትና በግልግል ጉዳዩ ውስጥ የታቀፉትን ፍሬ ነገሮች የሚገዙት ልዩ የውል አቀራረጽ ደንቦች መከበር አለባቸው።

የውሉን ጉዳይ ለግልግል ስምምነት የማቅረብን ችሎታ ያየን እንደሆነ ፣ (እላይ በንዑስ ክፍል "ሐ" የተገለጸውን ይመለከቷል) ተዋዋዩ ወገን በራ መብት እንዲኖረው የማስፈለጉ ጉዳይ የማይታለፍ ነው። "መብትን ያለዋጋ ለመስጠት የሚያስፈልገው ችሎታ" የሚለውን ኃይለ ቃል በሕጉ ማስቀመጥ ያስፈለገውም ለዚሁ ይመስላል። ይሁንና የውል አቀራረጹንም እስመልክቶ "መብትን ያለዋጋ ለመስጠት" የሚለው ኃይለ ቃል በፍትሐ ብሄሩ ሕግ ቁጥር 3326 (2) መጠቀሱ ግራ የሚያጋባ ነው ማለት ማጋነን አይሆንም። ይህን የሕግ አንቀጽ እንዳለ እንከተለው ብንል ዝቅ ብሎ እንደተቀመጠው የማይመስል ውጤት ላይ ያደርሰናል።

ለምሳሌም ያህል አለመግባባቱ የሚመለከተው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአንዱ ወገን ወደሌላው የሚተላለፍበትን ሁኔታ ነው እንበል። የማይንቀሳቀስን ንብረት ያለዋጋ (ማለትም በስጦታ) ማስተላለፍን የሚመለከቱ ውሎች በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ አሠራር ዓይነት መደረግ እንዳለባቸው ሕጉ ይደነግጋል።[37] በዚህም መሠረት ውሉ ስጦታ አድራጊው ራሱ የጻፈው ፣ ወይም እርሱ እየተናገረ ሌላ ማናቸውም ሰው የጻፈውና ስጦታ አድራጊውና አራት ምስክሮች የፈረሙበት እንዲሆን ይገባል ማለት ነው። በመሆኑም ይህን የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስተላለፍን በተመለከተ የሚነሳውን አለመግባባት ተዋዋዮቹ በግልግል ስምምነት ለመጨረስ ከፈለጉ ስምምነታቸውን እላይ በተገለጸው ሥርዓት መሠረት ማድረግ አለባቸው ማለት ነው። ይህም ማለት የግልግል ስምምነቱ በተዋዋዮቹ በራሳቸው ወይም እነሱ እየተናገሩ በሌላ ሰው መጻፍ አለበት፣ ተዋዋዮቹና አራት ምስክሮችም በላዩ ላይ ፊርማቸውን ማስቀመጥ አለባቸው፣ ማለት ነው። የሕግ አውጭው ፍላጎት ይህን ውጤት ለማግኘት መሆኑ ግን በአያሌው የሚያጠራጥር ነው።

በመሆኑም የግልግል ስምምነትን በተመለከተ መከተል የሚገባን የውል አቀራረጽ ሥርዓት የትኛው እንደሆነ በቅጡ ለይቶ ማስቀመጥ በጣሙን አዳጋች ነው። ይህም ቢሆን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ መብትን[38] ፣ በመርከብ ላይ ያለ መብትን[39] ፣ በንግድ መድበል ላይ ያለ መብትን[40] ፣ እንደዋስትና ያሉ የረዥም ጊዜ ግዴታን የሚያስከትሉ ጉዳዮችን[41] ፣ የመድን

---

[37] ቁጥር 2443 ፣ 881 883 ፍ.ሕ.

[38] ቁጥር 1723 ፍ.ሕ. በተጨማሪም በፍ/ቤት ወይም በውል አዋዋይ መመዝገብ አለበት።

[39] ቁጥር 7 የባህር ሕግ

[40] ቁጥር 152 የንግድ ሕግ

[41] ቁጥር 1725 (ሀ) ፍ.ሕ.

ውልን[42] እና መሰል ጉዳዮችን የሚያቅፉ ውሎች በጽሁፍ ተዘጋጅተው በሁለት ምስክሮች የተረጋገጡ መሆን እንዳለባቸው ሕጉ ያዛል።[43] እነዚህን ውሎች የሚመለከቱ ክርክሮችን በግልግል ስምምነት መጨረስ ካስፈለገ አስተማማኙና የሚመረጠው አሠራር ስምምነቱን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ሁለት እማኞች እንዲፈርሙበት ማድረጉ ነው። ነገር ግን እንደ ሽያጭ ውሎች ፣ የዕቃ ማጓጓዣ ውሎች ፣ (የባህር የማጓጓዣ ውሎችን ሳይጨምር)[44] እና የሥራ ተቋራጭ ውሎችን የመሳሰሉ ብዙ ዓይነት ውሎች ደግሞ በጽሁፍ መሆን አያስፈልጋቸውም። እነዚህን ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችንበግልግል መጨረስ ካስፈለገ የግልግል ስምምነቶች በቃል ሊደረጉ ይችላሉ የሚል አመለካከት በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ዘንድ አለ። ይሁንና ሽሚትሆፍ የተባሉት ጸሀፊ:-"የዚህ ዓይነት አሠራር የግልግል ስምምነቱን አተረጓጎምና ተግባራዊ አፈጻጸም አጠራጣሪ ያደርገዋል"[45] በማለት በትክክል እንዳስቀመጡት ሁሉ ስምምነቱን በቃል ማድረግ እምብዛም የሚመረጥ አሠራር አይደለም። በእነዚህም አጋጣሚዎች ተዋዋዮች ስምምነታቸውን በጽሁፍ የማድረግ ምርጫ አላቸው። ከዚህ የምንወስደው ሀሳብ በተዋዋዮችየተፈረመ ሰነድ ፣ በመሀከላቸው የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች ፣ አለበለዚያም በቴሌክስ ወይም በቴሌግራም የተደረጉ መልዕክቶች በዚህ ረገድ በቂ ተደርገው ሊወሰዱ መቻላቸውን ነው።[46]

የግልግል ስምምነት መኖሩን በማስረጃ ማረጋገጥ በሚያስፈልግበት ጊዜ የማስረዳት ሸክሙ ስምምነቱ አለ በሚለው ወገን ትከሻ ላይ ይወድቃል።[47] እንደግንኙነቱ ዓይነት ይህ ሕግ የሚጠይቀውን ሰነድ ፣ ወይም ሌሎች የጽሁፍ ማስረጃዎችን ፣ ወይም ምስክሮችን ወይም አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች የማቅረብ ሀላፊነት ይኖርበታል።[48]

የግልግል ስምምነት የሚደረግበት አኳኋን እንደተዋዋዮቹ ፍላጎት ይለያያል። ክርክሩ የተጀመረ ከሆነ አለመግባባታቸውን በሌላ ተጨማሪ ውል ለግልግል ለማቅረብ መስማማት ይችላሉ። ወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመት ክርክር የሆነ እንደሆነ ደግሞ ራሱን በቻለ

---

42 ቁጥር 1725 (ለ) ፍ.ሕ.

43 ቁጥር 1727 (2) ፍ.ሕ.

44 ቁጥር 134 የባህር ሕግ ፤

45 ክሊቭ ኤም ፣ <u>የሽሚትሆፍ የላኪነት ንግድ ፣ የኢንተርናሽናል ንግድ ህግና ልማድ</u> (ለንደን እስቲቨንስ እና ልጆቹ እ.ኤ.አ 1986) ስምንተኛው እትም ገጽ 583 ፣ በተግባር በጥንቃቄ የተረቀቀ በጽሁፍ የሆነ የግልግል ስምምነት መደረግ እንዳለበት እንመክራለን።

46 ተዋዋይ ወገኖች በግልጽ ስምምነቱን በልዩ ፎርም ለማድረግ ከተስማሙ ይህንኑ ፎርም ዓይነት መከተል አለባቸው። ቁጥር 1726 ፍ.ሕ.

47 ቁጥር 2001 (1) ፍ.ሕ.

48 ቁጥር 2002 ፍ.ሕ.

የውል ሰነድ ወይም በዋናው ውል ላይ ገልግሎ የሚመለከት ኃይለ ቃል አስተድመው በማስገባት ለግልግል የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ።[49]

## ክፍል ሁለት

## የግልግል ስምምነት ይዘት

### ሀ. ገላጋዮችን ስለመሰየም

የግልግል ስም ምነት ከሚ ይዛቸው ጉዳዮች የመጀመሪያዎቹ ገላጋይ አካል የሚ ቋቋም ባቸው የውለታ አንቀጾች ናቸው። (ይህ ገላጋይ አካል አንድ ግለሰብ ወይም ብዙ ሰዎች ያሉበት ሊሆን ይችላል።) በዚህ አኳኋን ተዋዋዮቹ ከዚህ በታች ከተመለከቱት አራት ዓይነት አሠራሮች አንዱን የመምረጥ መብት አላቸው።

1. በግልግል ስምምነቱ በራሱ ላይ ወይም ከስምምነቱ በኋላ ገላጋዮቹን በስም ማመልከት ይችላሉ።
2. ገላጋዮቹን በስም መጥቀስ ሳያስፈልጋቸው የአመራረጡን ሁኔታ በስምምነቱ መግለጽ ይችላሉ። (ገላጋይ የሚሰይምላቸውን አካል ማመልከት በዚህ ምድብ ይጠቃለላል።)
3. ጉዳዩ በሌሎች የተለመዱ የግልግል ሕጎች ወይም የግልግል ሥርዓቶች ይመራል በማለት ብቻም ሊወስኑ ይችላሉ።[50] ለምሳሌም በአለም የንግድ ምክር ቤት (አይ.ሲ.ሲ) ደንቦች፣ ወይም የተባበሩት መንግሥታት በሰየመው የዓለም የንግድ ሕግ ኮሚሲዮን የግልግል ደንቦች (ዩ.ኤን.ሲ.አይ.ቲ.አር.ኤ.ኤል) መሠረት ገልግሉ ይታያል ብለው ሊስማሙ ይችላሉ።
4. ገልግል መኖሩን በማመልከት ብቻ በመወሰን ስለገላጋዮች አሰያየም ምንም ዓይነት መግለጫ ሳይሰጡ ሊያልፉ ይችላሉ። በዚህ ጊዜም አግባብነት ያላቸው የፍትሐ ብሄር ሕግ የግልግል ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ።[51]

ምናልባት የተመረጡት ገላጋዮች በግናቸውም ምክንያት ተግባራቸውን ለማከናወን ያልቻሉ እንደሆነ ሌሎች ገላጋዮች ሊተኩ የሚችሉበትን ሥርዓትም አብረው ማስቀመጥ

---

49 ቁጥር 3328 ፍ.ሕ.

50 ቁጥር 3346 ፍ.ሕ.

51 ቁጥር 3331 3343

እንዳለባቸው መጠበቅ ተገቢ ይሆናል።[52] የዚህ ዓይነት ተንታቄ በገልገል ስምምነቱ ላይ አስቀድሞ ያልተደረገ እንደሆነ አሁንም ችግሩ የሚፈታው በፍትሐ ብሄር ሕጉ መሠረት ነው። ገላጋዮች የሚሰየሙበትንና የሚተኩበትን አሠራር በተመለከተ ከፍ ሲል ከገለጽኩት ውጭ ያሉትን ሌሎች ሁኔታዎች መመርመር ከዚህ ጽሁፍ ትኩረት ውጭ ነው። ይሁንና አንባቢዎችን በተጨማሪ የማሳሰበው ከሕጉ ጋር የማይጣጣሙ አንዳንድ የገልገል ኃይለ ቃላትን በምትመለከቱበት ጊዜ በእርጋታ እንድታልፉኝ ነው። ለአቀራረቡ አመችነት ሲልም እነዚህን ጉዳዮች ለየት ባሉ ንዑሳን አርእስት ለማቅረብ እገደዳለሁ። እነዚህም :-

ሀ) በኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት (ኢ.ቢ.ቢ.) አማካይነት የሚደረገው የገላጋዮች አሰያየም ሥርዓትና ፣

ለ) በገላጋዮች አሰያየም ጊዜ ተዋዋዮች በእኩል ደረጃ የማይታዩበትን ጊዜ ፣ ይጨምራሉ።

ሀ.1 <u>በኢትዮጵያ የንግድ ምክር ቤት አማካይነት የሚከናወነው የገላጋዮች አሰያየም ሥርዓት፥</u>

በብዙ ኢንተርናሽናል የሽያጭ ውሎች ላይ[53] አለመግባባቶች በሚነሱበት ጊዜ ጉዳዩ በኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት አማካይነት በገልገል እንዲወሰን የሚያደርጉ ኃይለ ቃላት ሠፍረው እናገኛለን። ይህም አሠራር የመነጨው የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ገልገልን የሚመለከቱ የራሱ ደንቦች እንዳሉትና በአሠራር የዳበረ ገላጋዮች የሚሰየሙበትና የሚነሱበት ሥርዓት እንዳለው ከመገመት ነው። ይሁንና ይህ አካል ገልገልን የሚመለከት ደንብና ገላጋዮች የሚሰየሙበት ሥርዓት የለውም። እንዲያውም የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት እስካሁን ድረስ ገላጋይ ለመሆን የሚያስችለው የእድገት ደረጃ ላይ አልደረሰም ማለትም ያስኬዳል። የኢትያጵያ ንግድ ምክር ቤት የተቋቋመው በአዋጅ ቁጥር 148/1970 ሲሆን ከተግባሩና ሀላፊነቱ አንዱ ፣

"ተዋዋይ ወገኖች ሲጠይቁ በንግድ ግንኙነት አንጻር የሚነሱትን አለመግባባቶች በገልገል ዳኝነት መፍታት " ነው።[54]

የአዋጁን ተግባራዊ አፈጻጸም አስመልክቶ ደንብና መመርያ ማውጣት የንግድ

---

[52] የሚመረጡት ሰዎች ለምሳሌ ትክክለኛ አእምሮ የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። የሚመረጡት የተፈጥሮ ሰዎች እንጂ ለምሳሌ እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ድርጅቶች መሆን የለባቸውም።

[53] ለምሳሌ ያህል የኢትዮጵያ አስመጪና ላኪ ኮርፖሬሽን የገዥ ትዕዛዝ ይመልከቱ። ፎርም ኮፒ/13 አንቀጽ 9። እንዲሁም የኢትዮጵያ የቅባት እህሎች ኤክስፖርት ኮርፖሬሽን የሽያጭ ውል ሞዴል ይመልከቱ።

[54] የአዋጁን አንቀጽ 6(5) ይመልከቱ ፣

ሚኒስቴር ሥልጣን ሲሆን [55] እስካሁን ድረስ ይህን በተመለከተ የወጡ ደንቦችና መመርያዎች የሉም።

ሕጉ በሚገባ አለመረቀቁም ሌላ ችግር አስከትሏል። ይህ እላይ የተጠቀሰው አዋጅ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት እንደገላጋይ አካል ሆኖ የመሥራት ሥልጣን እንዳለው ይገልጻል። ይሁንና ይህ አገላለጽ ግርማ ዘለቀ እንዳሉት፥ "በንግድ ዓለም ያሉትን የግልግል ደንቦችና መሠረተ ሀሳቦችን የማይከተል ነው። ምክንያቱም አሠራሩ እነዚህን ተቋሞች የክርክሩን አካሄድ እንዲከታተሉ ከማድረግ አልፎ በቀጥታ በክርክሩ የአወሳሰን ሂደት ውስጥ ስለሚያስገባቸው ነው።"[56] ይህ ጉዳይ አሁን ባለበት ደረጃ ማለት የሚቻለው የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት እንደማንኛውም አካል ሁሉ ገላጋይ እንዲሰይም በተዋዋዮቹ በተጠየቀ ጊዜ ይህንኑ ማድረግ ይችላል ማለት ብቻ ነው።

## ሀ.2 <u>በገላጋዮች አሰያየም ጊዜ በተዋዋዮች መሀል ሊኖር ስለሚችለው መበላለጥ፥</u>

ከግልግል ሕግ አዛዥ ደንቦች አንዱ በገላጋይ አሰያየም ረገድ የተዋዋዮች መብት በእኩል ደረጃ መጠበቅ እንዳለበት የሚደነግገው ነው። በገላጋዮች አሰያየም ወቅት ከተዋዋዮች ለአንዱ የተሻለ መብት የሚሠጥ የግልግል ስምምነት ዋጋ ያለው አይሆንም።[57] አንድ ተዋዋይ ወገን መሰየም የሚገባውን ገላጋይ አለመሰየሙ የተረጋገጠ እንደሆነ ሌላኛው ወገን ለብቻው የሚሰይመው ገላጋይ ተቀባይነት ይኖረዋል የሚል ኃይለ ቃል ያለው የግልግል ስምምነት ግን ዋጋ ይኖረዋል።[58] ከዚህ አልፎ ግን ገላጋይ የመሰየም መብትን ላንዱ ተዋዋይ ብቻ የሚሠጥ የግልግል ስምምነት ኃይለ ቃል አዛዥ ደንቦችን በግልጽ የሚጥስ ነውና ዋጋ አልባ ነው።[59]

---

55 በአዋጁ አንቀጽ 23 የንግድና ቀሪዝም ሚ/ር ተጠቅሷል።

56 ግርማ ዘለቀ፥ የንግድ የግልግል ዳኝነት የንግድ ኢኮኖሚያዊ አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ዳኝነት ውጭ ለመፍታት ስላለው አግራጭ፥ የሕግ ት/ቤት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፥ የመመረቂያ ጽሁፍ፥ እ.ኤ.አ. 1988፥ ገጽ 107፥ እንዲሁም በሺቶሪ ሚንጊ እና በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኮርፖሬሽን መካከል ባለው ክስ ኮርፖሬሽኑ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት እንዲያይለት ጠይቋል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት በዚሁ ተግባር አልሳተፍም በማለት ጥያቄውን አልተቀበለውም።

57 ቁጥር 3335 ፍ.ሕ.

58 የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሰራተኞች ጉዳት ካሳ ክፍያ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ናሙና አንቀጽ 14፥

59 የኢትዮጵያ አስመጪና ላኪ ኮርፖሬሽን ለአጠቃላይ ሸቀጦች አቅርቦት የሚያገለግል የናሙና የስምምነት ውል ቅንቀጾችና ሁኔታዎች አንቀጽ 26፥ በአሁኑ ጊዜ ግን አይሠራበትም።

## ለ) <u>የገላጋዮች ሥልጣን</u>

በግልግል ስምምነት ውስጥ መጠቀስ ያለበት ሁለተኛው ጉዳይ የገላጋዮችን ሥልጣን የሚገድበው አሠራር ነው። እርግጥ ተዋዋዮቹ ይህን የሚመለከት የውል አንቀጽ በግልግል ስምምነቱ ውስጥ ማስፈር አያስፈልጋቸውም። ምክንያቱም አንድ ጊዜ ገላጋይ ከተሰየመ በኋላ ሥራውን የሚመራውና ለክርክሩ ውሳኔ የሚሠጠው በሕግ በተመለከቱት ደንቦች መሠረት በመሆኑ ነው።[60] ከዚህ በመለስ የገላጋዩን ሥልጣን መገደብ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው ተዋዋዮቹ ሕግ ለገላጋዩ የሠጠውን ሥልጣን ለመቀነስ ወይም ገላጋዩ በሕግ ባለው ሥልጣን ላይ ተጨማሪ ሥልጣን ለመስጠት በሚፈልጉበት ጊዜ ብቻ ነው። ይህ የሥልጣን መገደብ አሠራር ተግባራዊ ሊሆን የሚችልባቸው አጋጣሚዎችና የአፈጻጸሙ ወሰንም ቀጥሎ ያሉት ናቸው።

1. በተዋዋዮቹ መሀል ያለው ክርክር የፍሬ ነገርና የሕግ ጥያቄዎች የሚያነሳ ሊሆን ይችላል። ሁለቱም ዓይነት ጥያቄዎች ከተነሱ ገላጋዩ ለጉዳዩ ውሳኔ መስጠት ያለበት በሕጉ መሠረት ነው። በአንዳንድ የውጭ ሀገር የሕግ ሥርዓቶች እንደምናየው[61] ተዋዋዮቹ ገላጋዩ በሕግ ብቻ ሳይገደብ ርትዕንና ሚዛናዊነትንም በመጨመር ጉዳዩን እንዲወስን ሥልጣን ሊሠጡት አይችሉም። ይህ መሠረታዊ የኢትዮጵያ ሕግ የፖሊሲ አመለካከት በባሕር ሕግም ላይ እንደሚከተለው ተንጸባርቋል።

> "በጭነት ሰነድ ላይ የተገለጸ የግልግል አንቀጽ በተዋዋይ ወገኖች መሀከል የሚነሳውን አለመግባባት በርትዕ ለመጨረስ በማናቸውም ሁኔታ ሥልጣን አይሠጣቸውም።"[62]

እርግጥ የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩ በግልግል ስምምነት እንዲታይ በሚያደርጉበት ጊዜ ገላጋዩ ነገሩን በሕግ ሳይሆን በአስተያየት እንዲወሰን መስማማት የሚችሉበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ይናገራል።[63] ይሁንና ይህ አገላለጽ ከመሠረታዊ ሕጎች ጋር በግልጽ የማይስማማ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።[64] በሌላ በኩል ደግሞ ተዋዋይ ወገኖቹ የገላጋዩን ሥልጣን ለማጥበብ ከፈለጉ በፍሬ ነገሩ ላይ ብቻ የደረሰበትን መደምደምያ እንዲገልጽ ሊያደርጉት ይችላሉ። ለምሳሌም ያህል የምድር መናወጽ ነበረ አልነበረም የሚለውን ፍሬ ነገር ብቻ አረጋግጦ

---

[60] ቁጥር 3325 (1) ፍ.ሕ. ቁጥር 317 - 318 ፍ.ሕ.ሥ.ሥ.ሕ.

[61] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 11 የተጠቀሱትን የረኔ ዴቪድ ጽሁፍ ገጽ 88

[62] ቁ. 209 የባህር ሕግ

[63] ቁጥር 317 (2) ፍ.ሕ.ሥ.ሥ.

[64] ሴድለር ፣ <u>የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ</u> ፣ በማለት የጻፉትን መጽሐፍ ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ አ.ኤ.አ በ1968 የታተመውን መጽሐፍ ገጽ 387 ይመልከቱ።

ይህ ፍሬ ነገር በሕገ ረገድ የሚያስከትለውን ውጤት ከመመልከት ሊያቅቡት ይችላሉ።[65]

2. ክርክሩን በሕግና በፍሬ ነገር እንጻር ተመልክቶ ከመወሰን የሰፋ መብት ተዋዋዮቹ ለገላጋዩ የሚሠጡበት ሌላው መንገድ ስለውሎች መሻሻል በፍትሐ ብሄር ሕጉ ያሉትን ደንቦች በመጠቀም ነው።።የሕጉ ቁጥር 1675 እንዲህ ይላል፥

> "የውሉ ስምምነት በሚደረግበት ጊዜ ወይም በኋላ የውሉን የዋጋ ሁኔታ የለወጠውንነገር በስምምነት ለማሻሻል የሚቻልበትን መንገድ ለመፈለግ ተዋዋዮቹወገኖች ነገራቸውን ወደ ዘመድ ዳኛ እንዲቀርብሊስማሙ ይችላሉ።"

ከዚህ የሕጉ ቁጥር መረዳት እንደሚቻለው ውልን ለማሻሻልና ለመለወጥ ያለ መብት አንድ ገላጋይ በመደበኛውአሠራር የተዋዋይወገኖችንየወደፊትግንኙነት ለመወሰንና ለመቆጣጠር ካለው ሥልጣን የተለየ ነው።

3. በውጭ የሕግ ሥርዓቶች የሚሠራበት አንድ የግልግል ሸንጎ የራሱን ሥልጣን ራሱ የሚወስንበትና "Kompetenz Kompetenz" እየተባለ የሚታወቀው አሠራርም[66] በተዋዋዮችሊገደብ የሚችል አፈጻጸም ነው። ተዋዋይ ወገኖቹ ይህ ገላጋይ በራሱ ሥልጣን ላይ ሊነሳ የሚችለውን ክርክር ራሱ ውሳኔ እንዲሠጥበት ሊያደርጉ ይችላሉ።[67] ለምሳሌም ያህል ከተዋዋዮቹ አንዱ ሸንጎው መያዝ ያለበት ሶስት ገላጋዮችን እንጅ አንድ ብቻ ሊሆን አይገባም የሚል መቃወምያ ሊያቀርብ ይችላል ፥ ወይም የቀረበው የክርክር ጭብጥ በግልግል ስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ አይደለም ብሎ ሊቃወም ይችላል። እላይ በተገለጸውየአሠራር ደንብ መሠረት የሆነ እንደሆነ የግልግል ሸንጎው በራሱ ሥልጣንላይ የተነሳውን የመቃወምያ ክርክር ራሱ ሊወስነው ይችላል ማለት ነው። ከዚህ ባሻገር ተዋዋዮቹ ራሱ የግልግል ስምምነቱ ሕጋዊ ውጤት አለው የለውም ተባብለው በሚወዛገቡበት ጊዜ ይህንንስ ሸንጎው ማየት ይችላል ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ነገር ግን ይህ የተፈቀደ ነው ብዬ ለመናገር ይከብደኛል።። ምነው ቢሉ አዛዥ የሆነው የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3330 (3) የሚከተለውን ያስቀምጣልና፥

> "የዘመድ ዳኛውበማናቸውም ሁኔታ የዘመድ ዳኛ ስምምነት ዋጋ ያለው ወይም የሌለው ነው ብሎ በሥልጣኑሊወስን አይችልም።"[68]

---

[65] ቁጥር 3325 (2) ፍ.ሕ.

[66] በኢንተርናሽናልንግድ የግልግል ዳኝነት የዩኒስትራል ሞዴል ህግ በተባበሩትመንግስታት ጽ/ቤት በቁጥር ኤ/ሲኤን 9/309 እ.ኤ.አ መጋቢት 25/1988 ገጽ 6

[67] ቁጥር 3320 (2) ፍ.ሕ.

[68] ኤልያስ ዳንኤል ዋናውንየፈረንሣይኛ ረቂቅ እንደሚከተለው ተርጉመውታል። "የግልግል ዳኛው በምንም ሁኔታ ቢሆን የግልግል ስምምነቱ ህጋዊ መሆን ወይም አለመሆኑን እንዲወስን አይጠይቅም።"

በዚህ ደንብ መንፈስ በግልግል ስምምነቱ በራሱ ውጤታማ መሆንና አለመሆን ረገድ የዳኝነት ሥልጣን ጥያቄ አከራካሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆን ለጉዳዩ ውሳኔ የሚሠጠው ፍርድ ቤት እንጅ የግልግል ሸንጎው አይደለም።[69] የዚህ ድንጋጌ ዓላማም ተቀባይነት ያለው ይመስላል። ምክንያቱም ይህን በተመለከተ የገላጋዩ ሥልጣን ካልተገደበ በግልግሉ ሂደት ሊከፈለው የሚገባውን የገላጋይነት አበል ላለማጣት ሲል የቀረበውን ጉዳይ ሁሉ የማየት ሥልጣን አለኝ ብሎ ወደመወሰን ያዘነብላልና ነው።

እዚህ ላይ ማጤን የሚገባን ይህን ጥያቄ ገላጋዩ ራሱ እንዲወስን ሥልጣን የሚሠጡት አንዳንድ ዓለም አቀፍ የግልግል ደንቦች በተለይም ደግሞ የዓለም የንግድ ምክር ቤት የግልግል ደንብ አንቀጽ 8 (3) እላይ ከተመለከተውና አዛዥ ከሆነው የፍትሐ ብሄር ሕጉ ደንብ ጋር የሚጻረሩ መሆናቸውን ነው።

## ሐ. <u>በግልግል ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮችን ስለመለየት</u> ፡

አንድ የግልግል ስምምነት ለግልግል የሚቀርበውን የክርክር ዓይነት ለይቶ እንዲያስቀምጥ ያስፈልጋል። በተለይም ለግልግል የሚቀርበው ጉዳይ ወደፊት የሚነሳ ክርክርን የሚመለከት ከሆነ (ማለትም ስምምነቱ ሲደረግ ክርክሩ የማይታወቅ ከሆነ) የግልግል ስምምነቱ ዋጋ የሚኖረው "በአንድ ውል ወይም በተለየ በመብት ገዥነት ላይ የሆነ እንደሆነ ነው" ሲል ሕጉ አዛዥ በሆነ ደንብ ይደነግጋል።[70]

ተዋዋዮቹ የፈለጉት "ጠባቡን የግልግል ኃይለ ቃል" ወይም "ሰፊውን የግልግል ኃይለ ቃል" ነው የሚለው ጥያቄ በመጀመርያ ደረጃ የሚመለሰው ራሳቸው በግልግል ስምምነቱ ላይ ባሠፈሩዋቸው ቃላት ነው። ለምሳሌም ያህል "በዚህ ውል ምክንያት የሚነሳ ክርክር" የሚሉና መሰል አነጋገሮች እንደጠባብ የግልግል ኃይለ ቃላት ይወሰዳሉ።[71] በሌላ አንጻር "ይህን ውል አስመልክቶ ወይም ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚነሱ ማናቸውም ክርክሮች" የሚሉና መሰል አነጋገሮች እንደሰፊ የግልግል ኃይለ ቃላት ይቆጠራሉ።[72] የዚህ ዓይነት ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢነሳ ፍርድ ቤቶች ይህን የአሠራር መስመር የሚከተሉ መሆናቸው እምብዛም አያጠራጥርም። ምክንያቱም አንድን የግልግል ስምምነት ዋጋ የሚሠጡት አከራካሪ የሆነው

---

69 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 45 የተጠቀሰው ጽሁፍ ገጽ 578 ይመልከቱ።

70 ቁጥር 3328/3 ፍ.ሕ.

71 አርተር ሾን ኔሀረን በጻፉት ኢንተርናሽናል የንግድ የግልግል ዳኝነት ጉዳዮችና ጽሁፎች (እ.ኤ.አ 1990) ከገጽ 189 190 ላይ የተጠቀሰውን በሚድትራንያን ኢንተርፐራይዝና በላንግዮንግ ኮርፖሬሽን መካከል እ.ኤ.አ በ1983 በአሜሪካ ሰርክዊት ፍርድ ቤት የነበረውን ክርክር ይመልከቱ።

72 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 45 በተጠቀሰው ጽሁፍ ገጽ 586 ይመልከቱ።

ጉዳይ "በግልግል ስምምነቱ የተሸፈነ" መሆኑን ካመኑ ብቻ ነው።[73]

ለክርክር ቀርቦ በነበረ በአንድ ጉዳይ ላይ በግልግል ስምምነት ላይ "ለውሉ ጉዳይ የሆነው ዕቃ የጠፋ ወይም የተበላሸ እንደሆነና በጥፋቱ ወይም በጉዳቱ መጠን ላይ አለመግባባት ከተነሳ ይኸው አለመግባባት .... (በግልግል ይወሰናል)" ተብሎ የተገለጸ አንጋገርን በማየት ገላጋዩ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለኝ ብሎ ደመደመ። ይሁንና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህ ገላጋይ ጉዳዩን አይቶ የሠጠውን ውሳኔ ሽሮታል። ፍርድ ቤቱ ይህን ያደረገው የመድን ሰጭውን የጉዳት ሀላፊነት የሚመለከቱ ክርክሮች በግልግል ስምምነቱ አለተሸፈኑም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው።[74]

ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት ለግልግል የሚቀርበውን ጉዳይ ለይቶ ማመልከቱ አስፈላጊ ነው። ይሁንና ይህ ብቻ በቂ አይደለም። ጉዳዩ በግልግል የሚታይ መሆኑን ማረጋገጥም የበለጠ አስፈላጊ ነው። ይህም የግልግሉን አጠቃላይ ሂደት ሕጋዊነት የሚመለከት ነው።[75] ይህ መሠረተ ሀሳብ ጠበቅ ብሎ የተቀመጠበት የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የሚከተለውን ይደነግጋል።

> "በግልግል እንዳይወሰንበሕግየተከለከለ ጉዳይ ወይም በፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር3331 እንደተነገረው ያለ ጉዳይ ሲሆን ለግልግል ዳኝነት አይቀርብም።"[76]

ይህ ድንጋጌ በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ሳይሆን በዋናውየፍትሐ ብሄር ሕግ ቢጠቀስ ኖሮ አለበለዝያም በፍትሐ ብሄር ሕጉ ውስጥ ይህን የመሰለ ድንጋጌ ቢኖር ኖሮ አከራካሪ ሆኖ ባልቀረበም ነበር። ዳሩ ግን ነገሩ አሁን ባለበት አኳኋን የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶች የሚያደርጓቸው ውሎች[77] ለግልግል ዳኝነት የሚቀርቡ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ጥያቄ

---

73 ቁጥር 3344 (1) ፍ.ሕ.

74 የጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 1386/79 የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከገብሩ አምደሚካኤልና ከለምለም አብርሀ ጋር የነበረውን ሙግት ይመልከቱ።

75 የተባበሩት መንግሥታት ስለ የውጭ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ተቀባይነትና አፈጻጸም ያሳለፈውን አለምዓቀፍ ስምምነት አንቀጽ 11 ፓራግራፍ 1 ይመልከቱ።

76 ቁጥር 315 (2) ፍ.ሕ.ሥ.ሥ.

77 "አንድ ውል እንዳስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ሆኖ የሚቆጠረው

ሀ. ሕግ ወይም ተዋዋዮች ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው ያሉት ሲሆን ፥

ለ. ውሉ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር የተያያዘና ለስራውም አፈጻጸም የተዋዋዩን የአስተዳደር መስሪያ ቤቱን ስራ ተካፋይነት ሳይቋረጥ የሚጠይቅ ሲሆን ፥

ሐ. በውሉ ውስጥ ለጠቅላላ ጥቅም አስቸኳይ በመሆናቸው ብቻና የግል ሰዎች በሚያደርጓቸው ውሎች ውስጥ የማይገኙ አንድ ወይም ብዙ ውለታዎች ያሉበት ሲሆን ነው።" ቁጥር 3132

እጅግ አወዛጋቢ ሆኖ ቆይቷል።[78]

በቅድምያ ለመግለጽ የምፈልገው የአስተዳደር ክፍል መሥርያ ቤቶች የሚያደርጓቸውን ውሎች የሚመለከተው የፍትሐ ብሄር ሕጉ አንቀጽ አሥራ ዘጠኝም ሆነ የገልገል ስምምነትን የሚመለከተው የዚሁ ሕግ አንቀጽ ሀያ ከዚህ ዓይነቱ ውል የሚነሳ ክርክር ለገልገል እንዳይቀርብ የማይከለክሉ መሆኑን ነው። ይህ ዓይነቱ ክልከላ የሕጉ አርቃቂ የሬኔ ዴቪድ ፍላጎትና ሀሳብ አይደለም እንጅ[79] ቢሆንማ ኖሮ የውጭ ባለሀብቶችን የሚያስበረግግ በሆነም ነበር። ይልቁንም አንድ ሰዉ ከፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3328[80] መንፈስ የሚረዳው ማንኛውም ክርክር ለገልገል ሊቀርብ መቻሉን ነው። ተዋዋዮች ለገልገል ሊያቀርቡ የሚችሏቸውን ጉዳዮች መገደብ የመዋዋል ነጻነታቸውን የሚነካ ነው። ሕግ አውጭው ይህን ለማድረግ ፍላጎቱ የነበረው ቢሆን ኖሮ መሠረታዊ ደንቦች በሠፈሩበት በፍትሐ ብሄር ሕጉ ውስጥ ባስቀመጠውም ነበር። ነገር ግን ሕግ አውጭው ይህን አላደረገም። አለማድረጉም ብቻ ሳይሆን እነዚህ ገደቦች ከዝያ በኋላ በወጣው የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ ይካተታሉ ብሎም አላሰበም። ያደረገው ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ውስጥ ይገባሉ በማለት መወሰን ነው። እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ "የግለሰቦች ጥያቄዎች በዳኝነት የሚታዩባቸው ፣ መብቶች ጥቅሞችና ግዴታዎች የሚረጋገጡባቸውና አግባብ ባለው አካል የሚተገበሩባቸው ናቸው።"[81] የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3345 ቀጥሎ ባለው አኳኋን የተቀረጸውም ለዚህ ነው።

"<u>ወደ ሥነ ሥርዓቱ ሕግ ስለመምራት</u>።

(1) የዘመድ ዳኝነት የሚከተለው ሥነ ሥርዓት በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ተደንግጓል።

(2) እንዲሁም የዘመድ ዳኛ ውሳኔ አፈጻጸምን ወይም ለዚሁ ውሳኔ ተቃራኒ የሆኑ አቤቱታዎችን ለሚመለከቱ ነገሮችም ይኸው ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል።"

የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ያረቀቀው አካል ግን በሥነ ሥርዓት ነክ ጉዳዮች ብቻ

---

78 ኢብራሂም እድሪስ ፣ <u>የአስተዳደር መ/ቤት ውሎችና የገልገል ዳኝነት ሕግ በኢትዮጵያ</u> ፣ የሕግ ፋኩልቲ (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ) ያልታተመ ጽሁፍ እ.ኤ.አ. በ1979 ገጽ 13

79 ሬኔ ዴቪድ ፣ የአስተዳደር መ/ቤት ውሎች በኢትዮጵያ የፍ/ሕግ ፣ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሄት ቅጽ 4 ቁጥር 1 (እ.ኤ.አ 1967) ገጽ 145 ቁጥር 3328

80 ቁጥር 3328 ፍ.ሕ. ፣ <u>የደረሰና ያልደረሰ ክርክር በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ ስለሚደረግ ስምምነት</u>፣
1. ለዘመድ ዳኛ የቀረበው ክርክር ቀድሞውኑ የነበረ ክርክር መሆን ይችላል ፣
2. እንደዚሁም ውል በሚደረግበት ጊዜ ተዋዋይ ወገኖች በአጋጣሚ በዚህ ውል ለመነሳት የሚችለውን ክርክር ለዘመድ ዳኛ ለማቅረብ ይችላሉ።

81 ሮበርት ኤ ሴድለር ፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 64 የተገለጸውን መጽሐፍ ገጽ 1 ይመልከቱ።

ሳይወሰን[82] ከመደበኛ ተግባሩ ወጣ በማለት የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶች ከሚያደርጓቸው ውሎች የሚነሱ ክርክሮች ለገላገል አይቀርቡም የሚል ክልከላ አስቀመጠ። ይህ ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ያሉትን መሠረታዊ ደንቦች በተለይም በቁጥር 3328 የተገለጸውን ድንጋጌ የሚጻረር ነው። በቀጣይነት የሚነሳው ጥያቄ የበላይነት ያለው የፍትሐ ብሔር ሕጉ ነው ወይስ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የሚለው ነው።[83] ለዚህ ምላሽ ለመስጠት ራሱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የፍትሐ ብሔር ሕጉን የበላይነት የተቀበለበትን አንድ አንቀጽ መጥቀሱ በቂ ነው።

> "በዚህ ምዕራፍ (ገላገልን በሚመለከተው) የተነገሩት ድንጋጌዎች በፍትሐ ብሔር ሕግ ከቁጥር 3345 እስከ 3346 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚነኩ አይደሉም።"[84]

በመሆኑም ከዚህ የምንደርስበት መደምደምያ የመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶች የሚያደርጓቸው ውሎች ወይም ከእነዚህ ውሎች የሚነሱ ክርክሮች ለገላገል ዳኝነት ሊቀርቡ የሚችሉ መሆናቸው ነው። (በነገራችን ላይ ይህ አመለካከት በጠቅላይ ፍርድ ቤትና በዓለም የገላገል ሸንጎ ተቀባይነት ያገኘ ነው።)[85]

በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 315 (2) ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ በመንግሥት የአስተዳደር መሥርያ ቤቶች ከሚደረጉ ውሎች የሚነሱ ክርክሮች ለገላገል ዳኝነት የሚቀርቡ አይደሉም የሚለውን አስተሳሰብ እንቀበል ብንል እንኳ ተግባራዊ አፈጻጸሙ ብዙም ፋይዳ ያለው አይደለም። ለምን ቢባል በሀገርም ሆነ በውጭ ሀገር ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ሊያደርጉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ በርካታ የመንግሥት አስተዳደር መሥርያ ቤቶች ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚነሱ አለመግባባቶችን በገላገል ለመጨረስ የሚያስችል ሥልጣን በሕግ የተሠጣቸው በመሆኑ ነው። ቀጥሎ ያሉትን መሥርያ ቤቶች ለአብነት ያህል መጥቀስ

---

82 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 78 የተጠቀሰው የኢብራሂም ኢድሪስ ጽሁፍ ውስጥ እንደገለጹት የፍትሐ ብሔር ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 315 (2) የሚገልጸው ስለዘመድ ዳኞች ችሎታ ማጣት ሲሆን ይህም የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ መሆኑን ነው። ይህ ክርክር ግን ተቀባይነት ያለው አይመስለኝም። የዚሁ ጽሁፍ ገጽ 14 ይመልከቱ።

83 በውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣንና በኩንዳን ሲንግ መሀከል በመዝገብ ቁጥር 688/79 በተካሄደው ክርክር ፍርድ ቤቱ የፍ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ.315 (2) ከፍ.ሕ.ቁ. 3345 ጋር ሲገናዘብ የተጣጣመ በመሆኑ ይህ ግንዛቤ ከቁጥር 3328 ጋር ከተጋጨ የመጀመርያው የበላይነት ይኖረዋል ብሎ ሀሳብ ሠጥቷል። ይሁንና ፍ/ቤቱ እዚህ መደምደምያ ላይ ሲደርስ በፍ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ.315 (4) የተመለከተውን ጭራሹን የዘነጋ ይመስላል።

84 ቁጥር 315 (4) ፍ.ሕ.ሥ.ሥ.

85 የጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 1144/67 ፣ በኢትዮ ማርኬቲንግ ሊሚትድና በማስታወቂያ ሚኒስቴር የነበረው ክርክር ፣ በኩንዳንሲንግ እና በውሀና ፍሳሽ ባለሥልጣን መካከል ያለው ክርክር ፣ የኢንተርናሽናል ንግድ ምክር ቤት የገላገል ዳኝነት እ.ኤ.አ 1987 የታየ፣

ይቻላል። የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣[86] የባህር ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣[87] የአየር ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣[88] የኢትዮጵያ ትራንስፖርት ኮንስትራክሺን ባለሥልጣን፣[89] የኢትዮጵያ ውሀ ሥራዎች ኮንስትራክሺን ባለሥልጣን፣[90] እና የኢትዮጵያ ሕንፃ ኮንስትራክሺን ባለሥልጣን።[91] እነዚህ ተቋሞች የተመሠረቱባቸው አዋጆች መሥርያ ቤቶቹ አለመግባባቶችን በግልግል እንዲጨርሱ ሥልጣን በሚሠጡበት ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ ያለውን ክልከላ አሻሽለውታል ማለት ይቻላል። ይህን ካልኩ በኋላ ሌሎችስ ለግልግል ሊቀርቡ የማይችሉ ጉዳዮች የሉም ወይ ወደሚለው ጥያቄ እሸጋገራለሁ።

እንደፈረንሣይ ባሉ አንዳንድ ሀገሮች ሕግጋት ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮች ለግልግል የሚቀርቡ አይደሉም ተብሎ ተመልክቷል። ከእነዚህም ውስጥ የሰዎችን ማንነትና ሁኔታ፣ ችሎታና ፍቺ እንደዚሁም ፀረ-ሞኖፖል ደንቦችን የሚመለከቱት ይገኛሉ።[92] በቦሊቪያ ውስጥ የመስተዳድሩ አካል ከሚፈጽማቸው ተግባሮች የሚነሱ ክርክሮች ሁሉ በግልግል እንዳይታዩ ተከልክሏል።[93] በኢትዮጵያ ውስጥ ግን እላይ ከጠቀስኩት የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ደንብ በስተቀር የዚህ ዓይነት ጉዳይ ለግልግል እንዳይቀርብ የሚከለክል ሕግ በበኩሌ አላየሁም። አንዳንድ ግምቶችን መውሰድ ግን ይቻላል።

ንብረት ማስለቀቅን የሚመለከቱት የፍትሐ ብሄር ሕጉ ደንቦች (ከቁጥር 1460 እስከ 1488 የተመለከቱት) የተለቀቀውን ንብረት ግምትና ካሣ አከፋፈል አስመልክቶ በመጠኑ ላይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩ በሽምግልና አገማመት ከሚሰዮን ሊወሰን እንደሚችል ይደነግጋሉ። ከዚህ የምንረዳው ዋናው የንብረት ማስለቀቅ ተግባር ግን ለግልግል እንደማይቀርብ ነው። ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አንድ ወንድና አንዲት ሴት አብረው የሚኖሩ በሆነበት ጊዜ ይህ ግንኙነት መኖር አለመኖሩንና በዚሁ ግንኙነት ምክንያት የሚነሱትን ክርክሮች ተመልክተው ውሳኔ ለመሥጠት ሥልጣን ያላቸው ዳኞች ብቻ እንደሆኑ የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 730 ያመለክታል። ከዚህም የምንገነዘበው ይህን ዓይነት ጉዳዮች ለግልግል የማይቀርቡ መሆናቸውን ነው። ይሁንና

---

86 የፔትሮሊየም ስራዎች አዋጅ ቁጥር 296/1978 አንቀጽ 25 እና 27 የአዋጅ አንቀጽ 27 ተቃራኒ የሆኑትን ህጎች ይሽራል።

87 አዋጅ ቁጥር 139/1970 ቁጥር 7(19)

88 አዋጅ ቁጥር 111/1969 ቁጥር 8(18)

89 አዋጅ ቁጥር 189/1972 ቁጥር 8(19)

90 አዋጅ ቁጥር 190/1972 ቁጥር 6(13)

91 አዋጅ ቁጥር 191/1972 ቁጥር 8(14)

92 ረኔ ዴቪድ፣ በኢንተርናሽናል ንግድ የግልግል ዳኝነት፣ ገጽ 187

93 ከላይ የተመለከተው ፅሁፍ ገጽ 177

የእነዚህ ግምቶች ጥንካሬ የሚለካው አሁን አለን ለማለት በማንደፍረው ነገር ግን ወደፊት እየተከሰቱ ሊሄዱ በሚችሉ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችና የሕግ አስተሳሰቦች ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## የግልግል ስምምነት ውጤት

### ሀ. የስምምነቱ አስገዳጅነት ባህርይና ተፈጻሚነት፣

በመሀከላቸው የሚነሳውን ክርክር በግልግል ለመጨረስ ተዋዋይ ወገኖች የሚያደርጉት ስምምነት የሕግ ያህል ዋጋ ተሠጥቶት ይገደዱበታል።[94] የስምምነታቸውን አስገዳጅ ባህርይ በመረዳት ሁለቱም ወገኖች ክርክሩን እነሱው ራሳቸው ለሰየሙት ገላጋይ ሸንጎ ካቀረቡት ይህ አካል ልክ እንደ ፍርድ ቤት ሁሉ ጉዳዩን መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ይሠጣል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አንዱ ወገን በግልግል ስምምነቱ ከተመለከተው ውጭ ክርክሩን በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው እንደሆነ ሌላው ወገን ስምምነቱ ቀሪ እንደሆነ በመገመት በዝያው በኩል የራሱን መከላከያ የማቅረብ ምርጫ አለው።[95]

የስምምነቱ አስገዳጅ ባህርይና ተፈጻሚነት ጉዳይ ጎልቶ የሚወጣው አንደኛው ወገን ስምምነቱን ሳይከተል በቀጥታ በፍርድ ቤት በኩል ክስ ሲመሠረትና ሌላው ወገን ደግሞ ክርክሩ በግልግል እንዲታይ በሚፈልግበት ጊዜ ነው።ከዚህ ጋር በተያያዘ "ባለመፈጸም ስለሚደረግ ቅጣት" በሚል ርዕስ ሥር የተካተተው የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3344(1) የሚከተለውን ይደነግጋል።

> ለዘመድ ዳኝነት ስምምነት ካደረጉት አንዱ ወገን በዚህ ስምምነት ውስጥ ለተመለከተ ክርክር ወደ ዳኞች የሄደ፣ ወይም የዘመድ ዳኞችን ለማደራጀት አስፈላጊ የሆኑትን ተግባር ችለመፈጸም እምቢ ያለ፣ ወይም በዘመድ ዳኛ ስምምነት የተያዙ አይደለሁም ባይ የሆነ እንደሆነ፣ ሌላው ወገን እንደመረጠው በዘመድ ዳኝነት የተደረገውን ስምምነት እንዲፈጸም ለማስገደድ ወይም በተለይ ለተነሳው ክርክር ስምምነቱ ቀሪ እንደሆነ ለመቁጠር ይችላል።

ከላይ የተገለጸውን ምሳሌያዊ ሁኔታ ያየን እንደሆነ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የቀረበውን ጉዳይ እናይም ብለው ጉዳዩ በስምምነቱ መሠረት በግልግል እንዲታይ የመመለስ ግዴታ አለባቸው። ይህ እንደእንግሊዝ ፍርድ ቤቶች የቀረበውን ጉዳይ ራሳቸው ለማየት ወይም ላለማየት ሕግ ምርጫ ከሚሠጣቸው ፍርድ ቤቶች አሠራር የተለየ ነው።[96] ፍርድ ቤቶቻችን በተግባር እያከናወኑ ያሉትም

---

94 ቁጥር 1731(1)፣ ፍ.ሕ.

95 ቁጥር 3344(1)፣ ፍ.ሕ.

96 ሬኔ ዴቪድ፣ ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 92 የተመለከተው፣ ገጽ 210-211

ይህንኑ ነው። በእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት (እሰገድ) እና በኢትዮጵያ አግልጋሜትድ መሀከል ተካሂዶ በነበረ አንድ ክርክር[97] እርሻ ሰብል በተከሳሹ ላይ ብር አሥር ሚሊዮን አካባቢ የሚደርስ ክስ በከፍተኛው ፍርድ ቤት መሠረተበት። ተከሳሹ ድርጅት ደግሞ ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ አስቀድሞ ስምምነት የተደረሰ ስለሆነ ወደዝያው ተመልሶ እንዲታይ ይታዘዝ የሚል ክርክር በመጀመርያ ደረጃ መቃወምያ መልክ አቀረበ ፥ ፍርድ ቤቱም የተከሳሹን መቃወምያ በመቀበል ጉዳዩ በግልግል የሚታይ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶ ግራ ቀኙን አሰናበታቸው።በዚህ ውሳኔ ጊዜ ግን የተባለው የግልግል ሸንጎ ገና አልተቋቋመም ነበር።

## ለ. አንዳንድ ቅድመሁኔታዎች፥

ክርክሩንወደግልግል ከመምራቱ በፊት አንድ ፍርድ ቤት ቀጥሎ ያሉትን ጉዳዮችማጣራት ይኖርበታል። እነዚህም፥ ሀ) ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ለማየት የሚያስችል የፀና ስምምነት መኖሩን፥[98] ለ) የግልግል ስምምነቱ የተያዘውን ክርክር የሚሸፍን መሆኑን፥ እና (ሐ) የግልግል ስምምነቱ ያልተቋረጠ መሆኑ፥ ናቸው። ቀጥለን እንመለከታቸዋለን።

1. "ክሱ በግልግል ዳኝነት የሚታይ ነው"[99] ወይም የክርክሩ ጭብጥ በግልግል ታይቶ እንዲወሰን የሚያደርግ ስምምነት አለ የሚለውን የመጀመርያ ደረጃ መቃወምያ የሚያነሳው ተከሳሽ ይህን መቃወምያውን ክርክሩ እንደተጀመረ እንዲያነሳው ያስፈልጋል። አለበለዝያ መቃወምያ የማንሳት መብቱን እንደተወው ይቆጠራል።[100] ከዚህ በኋላ ከሳሹ በበኩሉ በሚሠጠው የመልስ መልስ የግልግል ስምምነት የሚባል ነገር ከቶውኑም አልተደረገም ፥ ወይም ስምምነቱ በሕግ ፊት የሚጸና አይደለም ፥ ብሉ የተከራከረ እንደሆነ ጉዳዩ ወደግልግል የሚመራው በዚህ የከሳሹ ምላሽ ላይ ፍርድ ቤቱ አሉታዊ ውሳኔ የሠጠ እንደሆነ ብቻ ነው። በተለይም እንከን የምላቸው የግልግል ኃይለ ቃላት በስምምነቱ ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ ይህን ጉዳይ መመርመሩ ውስብስብ ሊሆን ይችላል። ይህን ፍሬ ነገር እ.ኤ.አ. በ1984 በአትክልትና ፍራ ፍሬ ልማት ኮርፖሬሽንና ሺቶሪ ማንጊ በተባለ ድርጅት መሀል በተደረገ ውል፥ እንደዚሁም እ.ኤ.አ. በ1987 በኢትሚክስና በሳፊት መሀል በተደረገ ሌላ ውል ውስጥ የተከሰቱ ሁኔታዎችን እንደ ምሳሌ በመጥቀስ ላብራራው።

በአትክልትና ፍራ ፍሬና በማንጊ መካከል በተደረገው ውል ግልግልን የሚመለከተው አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል።

---

97 የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሄር መዝገብ ቁጥር 1101/82

98 የፍ.ሕ.ቁጥር 1678፥ 1731፥ 3344(1) ንባብ

99 ቁጥር 244(2)(ለ) ፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ

100 ቁጥር 244(3) ፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.

> <u>አንቀጽ አሥር፣ስለገላገል፣</u>
> በዚህ ውል ምክንያት አለመግባባት የተነሳእንደሆነ አለመግባባቱ አዲስ አበባ በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ገላጋይነት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ውሳኔ ያገኛል።

ውሉ አድር የተጠበቀው ክርክር ከተነሳ በኋላ የአትክልትና ፍራ ፍሬ ልማት ኮርፖሬሽን የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ይህን ጉዳይ እንዲያይ በገላጋይነት የተሰየመ ስለሆነ ክርክሩ በዝያው በኩል ሊታይ ይገባዋል በማለት አጥብቆ ተሟገተ። እስኪ ነገሩን ከሌላው ገጽታ እንየው። ይህን የገላገል ኃይለ ቃል ባለመከተል አትክልትና ፍራፍሬ በጉዳዩ ላይ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል እንበል። ማንኪ ደግሞ ይህን ተቃውሞ በገላገል ስምምነቱ መሠረት ጉዳዩ በፍርድ ቤት በኩል የሚታይ አይደለም ብሎ ተከራከሯል እንበል። አትክልትና ፍራፍሬ ይህን ፍሬ ነገር ሊክድ አይችልም። ስምምነቱ መደረጉ ሐቅ ነውና። በዚህ ረገድ አትክልትና ፍራፍሬ ሊያነሳው የሚችለው መከራከሪያ አንድ ብቻ ነው። ይህም የገላገል ኃይለ ቃሉ ገላጋዩን የተፈጥሮ ሰው በማድረግ ፋንታ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል እንዲሆን የሚያደርግ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፤ ወይም የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት የገላጋይነት ሀላፊነቱን አልተቀበልም ብሎ የገለጸ ስለሆነ የገላገል ስምምነቱ ቀሪ ሆኗል የሚለው ነው። የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ይህን መከራከርያ በመቀበል ጉዳዩን ተመልክተው የሚወስኑ መሆኑ ፣ አለበለዝያም አንዳንድ የውጭ ሀገር ፍርድ ቤቶች እንደሚያደርጉት "የግራ ቀኙ ተዋዋዮች ዐቢይ ፍላጎት የሚነሳ ክርክርን በገላገል ለመጨረስ እንጅ ገላገሉ በአንድ የተለየ ገላጋይ አካል ብቻ እንዲደረግ አይደለም"[101] የሚል ግምት በመውሰድ ሌሎች ገላጋዮች እንዲያዩት የሚያደርጉ መሆን አለመሆናቸው ገና የማይታወቅ ነው። ምክንያቱም ይህን አስመልክቶ እስካሁን የቀረበ ክርክር የለምና ነው።

በኢትሚክስና በሳፈት መሀከል ተደርጎ በነበረው ሌላ ውል ውስጥ የሠፈረው የገላገል ኃይለ ቃል ደግሞ ይህ ነው።

> <u>አንቀጽ 16</u>
> <u>ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ</u>
> የዚህን ውል አተረጓጎም ወይም ይህን ውል በሚመለከት በማናቸውም ጉዳይ፣ ወይም ከዚህ ውል ጋር በተያያዙና ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ በገዥውና በአቅራቢዎቹ መሀከል ማናቸውም ዓይነት ክርክር ወይም የአመለካከት ልዩነት የተነሳ እንደሆነ በቅድምያ በሁለቱ ወገኖች መሀል በመግባባት በሚደረግ ውይይት መፍትሄ እንዲያገኝ ይደረጋል፤ ይህ ያልሆነ እንደሆነ ደግሞ ጉዳዩ ፓሪስ በሚገኘው ዓለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት በኩል እንዲታይ ይደረጋል።

በመጀመርያው ምሳሌ እንዳየነው ሁሉ ኢትሚክስ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ክስ በሚመሠርትበት ጊዜ ሳፈት ደግሞ ይህን ተቃውሞ ጉዳዩ በገላገል የሚታይ ነው ብሎ ተከራከሯል እንበል። በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አመለካከት ለሳፈት ይህ ክርክር የሚያዋጣው አይደለም። ምክንያቱም መጀመርያውኑ ጉዳዩን በገላገል ለመጨረስ የተደረገ ስምምነት

---

[101] አስትራ ፋትዌር ኢንደስተሪና ሐርዊን ኢንተርናሽናል የተከራከሩበት ጉዳይ፣ (የዩናይትድ እስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ. 1978) ከኢ.ሾን ሚሀረን ገጽ 203.

ባለመኖሩ ነው። ግልግል የሚለው ቃል በዚህ በተጠቀሰው የውሉ አንቀጽ ውስጥ ተለይቶ በግልጽ አልተቀመጠም። አንድ ፍርድ ቤት የግልግል ስምምነትን ተፈጻሚ የሚያደርገው ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ በተዋዋዮቹ መሀል የተደረገ ውል ሲኖር ብቻ ነው።

2. ሁለተኛው ሁኔታ ደግሞ የግልግል ስምምነቱ የሚመሠረትበትን የውል ጉዳይ የሚመለከት ነው። አንድ ፍርድ ቤት የሚቀርብለትን የግልግል ስምምነት ውጤታማ የሚያደርገው የተያዘው ክርክር በስምምነቱ ውስጥ የሚሸፈን መሆኑን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው። ክፍ ብየ ጠቆም ካደረግሁትና የመድን ድርጅት ገብሩና ለምለም ከተባሉ ግለሰቦች ጋር በነበረው አንድ የመድን ውልን በሚመለከት ክርክር በመድን ውሉ ላይ የሠፈረው የግልግል ኃይለ ቃል "የመድን ሽፋን የተሠጠው ዕቃ የጠፋ ወይም የተበላሸ እንደሆነ የጠፋውን ወይም የተበላሸውን ዕቃ መጠን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክር" በግልግል እንዲታይ የሚያደርግ ነበር። ክርክር ከተነሳ በኋላ ግን መድን ሰጭው የገላጋዩን ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ተቃወመ። ለዚህ ያቀረበው ምክንያት የሀላፊነቱ ጉዳይ በግልግል እንዲታይ የተደረሰ ስምምነት አልነበረም የሚል ነው። በዚህ ጉዳይ የያዝነውን ፍሬ ነገር የበለጠ ለማብራራት እስኪ የዚህንም ምሳሌ ሌላ ገጽታ እንመርምረው። ክስ ያቀረቡት ገብሩና ለምለም ናቸው እንበል። የመድን ድርጅት ደግሞ ክሱን ተቃውሞ ጉዳዩ ወደግልግል እንዲመራ ጠይቋል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ይዘት በአግባቡ ለይቶ ካወቀ በኋላ ልክ በመጀመርያው ሁኔታ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዳደረገው ሁሉ የጉዳት አላፊነትን የሚመለከተው የከሳሽ ጥያቄ በግልገል ስምምነቱ ያልተሸፈነ በመሆኑ የተከሳሹን መቃወምያ ውድቅ በማድረግ ጉዳዩን ራሱ ተመልክቶ ይወስነዋል ማለት ነው።[102]

3. ሦስተኛው ሁኔታ የግልግል ስምምነት ቀሪ የማይሆንባቸውን አጋጣሚዎች ይመለከታል። ቀሪ የሆነ የግልግል ስምምነት ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም። አንድ የግልግል ስምምነት ቀሪ ሆኗል የሚለውን ፍሬ ነገር ማስረዳት ያለበት ይኸ ስምምነት ቀርቷል ብሎ የሚከራከረው ወገን ነው። አብዛኛውን ጊዜ ይህን እንዲያደርግ የሚጠበቀው ክርክሩን በቀጥታ ለፍርድ ቤት ያቀረበው ከሳሹ ወገን ነው። ከሚከተሉት ነጥቦች አንዱ እንኳ መኖሩ ከተረጋገጠ ለግልግል ስምምነት መቅረት መነሻ ይሆናል።

ሀ) በግልግል ስምምነቱ የተሰየመው ገላጋይ ተግባሩን ያላከናወነ እንደሆነ፣[103]

ለ) በስምምነቱ መሠረት ገላጋይ ከመምረጡ በፊት ከተዋዋዮቹ አንዱ የሞተ እንደሆነ፣[104] እና

ሐ) በግልግል ስምምነቱ መሠረት ጉዳዩ ይታይ የሚለው ተዋዋይ ራሱ ክሱን በፍርድ ቤት

---

[102] በተጨማሪ የሚከተለው ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል 'ፍርድ ቤቱ የሀላፊነትን ሁኔታን በኢንሹራንሱ ላይ ከወሰነ በኋላ የሀላፊነቱን መጠን በተመለከተ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ለማስተላለፍ ይችላልን?" የሚለው ነው።

[103] ቁጥር 3337(1)የፍ.ሕ.

[104] ከፍ.ሕ. ቁጥር 3338 ንባብ የሚገኘው ግንዛቤ

የመሠረተ እንደሆነ (መብት ቀሪ እንዳይሆን የሚነሱ ጊዜያዊ ተያቄዎችን አይመለከትም) ወይም የግልግሉ ሂደት እንዳይቀጥል እምቢተኝነት ያሳየ እንደሆነ፣[105]

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ለመኖራቸው ፍርድ ቤቱ እርግጠኛ የሆነ እንደሆነ ተከሳሹ ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ የሚያቀርበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ክርክሩ በዝያው በኩል እንዲታይ ለማዘዝ ይችላል። አለበለዝያ ግን የከሳሹን ክርክር ባለመቀበል ጉዳዩ በስምምነቱ መሠረት እንዲያልቅ ወደሚመለከተው ገላጋይ አካል ይመራዋል።

## ክፍል አራት

## ተፈጻሚ ስለሚሆነው ሕግ

### ሀ. ጥቂት ቀዳሚ የአስተያየት ነጥቦች

በግልግል የሚታየው ክርክር በየትኛው ሀገር ሕግ መሠረት ይታያል የሚለው ጥያቄ ሀገር ውስጥ ተጀምረው እዝያው የሚያልቁ የግልግል ጉዳዮችን ሳይሆን ዓለም አቀፍ ባህርይ ያላቸውን የግልግል ጉዳዮች የሚመለከት ነው። ይህ የኋለኛው ሁኔታ በተለያዩ ሀገሮች የሚኖሩ ተዋዋይ ወገኖችን ጉዳይ ይዳስሳል። ይህን የሚሸፍነውና "የሕጎችን ግጭት የሚመለከት ሕግ" አንዳንድ ጊዜም "ዓለም አቀፍ የግል ሕግ" እየተባለ የሚታወቀው የሕግ ዘርፍ አፈጻጸም በዚህ ረገድ የዳበረ ሕግ ባላቸው ሀገሮችም እንኳ ብዙ ጊዜ አሳሳችና አስቸጋሪ ነው። በኛ ሀገር ደግሞ የበለጠ ውስብስብ ነው። ምክንያቱም፣

1) የኛ የግልግል ሕግ ደንቦች የተቀረጹት በአመዛኙ ሀገር ውስጥ ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ለመስጠት ስለሚመስሉ፣
2) የሕጎችን ግጭት የሚመለከት ሕግ በኢትዮጵያ የሌለ በመሆኑ፣[106] እና
3) ጉዳዩን በተመለከተ እስካሁን በፍርድ ቤት ውሳኔ የዳበሩ ምሳሌያዊ አሠራሮች፣ ባለመኖራቸው ነው።

በዚህም የተነሳ ይህን ፍሬ ነገር አስመልክቶ የምሠጠው አስተያየት ሚስተር ሲድለር

---

[105] ቁጥር 3344(1) እና (2)ፍ.ሕ.

[106] ሮበርት አለን ሲድለር <u>በኢትዮጵያ ውስጥ የሕጎች ግጭት፣</u> አዲስ አበባ፣ በቀ.ኃ.ሥ.ዩኒቨርስቲ ሕግ ፋኩልቲ እ.ኤ.አ. በ1965 የታተመ፣ ገጽ 4፣

ስለዚሁ ጉዳይ በጻፉት ጽሁፍ፥[107] እና በአንዳንድ የውጭ ሀገር ፍርዶች ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

ዓለም አቀፍ ባህርይ ላላቸው የገልገል ጉዳዮች የትኛውን ሕግ ተፈጻሚ ማድረግ ይኖርብናል የሚለው ጥያቄ ሦስት ልዩ ልዩ ዘርፎችን የሚዳስስ ነው። በመጀመርያ ዋናው የንግድ ግንኙነት የተደረገበት ዐቢይ ውል አለ። ውሉ የሸቀጦችን ሽያጭ፥ ውክልናን፥ የሥራ ተቋራጭነት ስምምነትን፥ የጋራ ልማት ሥራን፥ የዕቃ ማጓጓዝን፥ ...ወዘተ፥ የሚመለከት ሊሆን ይችላል። በሁለተኛ ደረጃ የዋናው ውል አንድ አካል በመሆን የገባው ወይም ራሱን በቻለ ሌላ ውል የተደረገው የገልገል ስምምነት ይኖራል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘው አሠራር ይህ ስምምነት ከዋናው ውል ተለይቶ ራሱን ችሎ እንደቆመ ሌላ ውል ተደርጎ ይወሰዳል።[108] በዚህም መሠረት የዋናው ውል ውድቅ መደረግ ብቻውን የገልገል ስምምነቱን ዋጋ አያሳጣውም ማለት ነው። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የገልገል ስምምነቱ የሚካሄድበት ሥርዓት አለ። አብዛኛውን ጊዜ ለሶስቱም ዘርፎች ተፈጻሚ የሚሆነው አንድ ሕግ ነው።[109]ነገር ግን አልፎ አልፎ በሚከሰቱ አጋጣሚዎች የተለያዩ ሕጎች ተፈጻሚ የሚደረጉባቸው ሁኔታዎች አሉ።

ለምሳሌ እንግሊዝ ሀገር ታይቶ በነበረ ጉዳይ (ቪስካውንት ዲልሆርን የተባሉት ዳኛ በሠጡት ፍርድ) የሚከተለው ተወስኗል:-

> "...ስለሆነም በአንድ የገልገል ኃይለታል ተዋዋዮቹ ጉዳዩ በእንግሊዝ ሕግ መሠረት ስዊትዘርላንድ ውስጥ እንዲታይ ከተስማሙ የእንግሊዝ ሕግ የገልገል ስምምነቱን ተቀባይነት፥ ትርጉምና ውጤት በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚደረግ ሲሆን የገልገል ሽምግልናውን ሂደትና ሥርዓት በተመለከተ ደግሞ የስዊዝ ሕግ ሥራ ላይ ይውላል።..."[110]

በሌላ ጉዳይ ላይም ፥ (ሎርድ ዳኒንግ የሚባሉ ዳኛ በሠጡት ፍርድ)

> "የውሉን አተረጓጎምና ውጤት የሚገዛው የእንግሊዝ ሕግ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ደርሰናል። የኩዌት ወይም የሌላ ሀገር ሕግ ደግሞ ገልገሉ በሚመራበት ሥርዓት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የዚህ ዓይነቱ ልዩነትም በሚገባ የታወቀ አሠራር ነው።"[111]

የዚህን ክፍል ትኩረት ወደሚጠይቀው ወደዓለም አቀፍ የገልገል ስምምነት መለስ

---

[107] ከላይ የቀረበውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

[108] ከላይ በቁጥር 92 የግርጌ ማስዋወሻ የቀረበውን ጽሁፍ ገጽ 193 ይመልከቱ።

[109] ከላይ በተራ ቁጥር 45 የተመለከተውን ጽሁፍ ገጸ 182 ይመልከቱ።

[110] ከላይ በተራ ቁጥር 10 የግርጌ ማስታወሻ ጽሁፍ ክፍል 3.2.9 በጀምስ ሚለርና በዊትወርዝ መካከል የነበረውን ክስ ይመልከቱ።

[111] ከላይ በተራ ቁጥር 110 የግርጌ ማስታወሻ ውስጥ በተጠቀሰው ጽሁፍ ክፍል 3.2.11 በኢንተርናሽናል ታንከና በኩዌት አሺየሽን መካከል የነበረውን ክስ ይመልከቱ።

በምንልበት ጊዜ ተዋዋይ ወገኖቹ በሌላ አኳኋን የተለየ ሕግ ተፈጻሚ የሚሆንበትን መንገድ ለማወቅ በግልጽ ካላስቀመጡ በተለመደው አሠራር ተፈጻሚ የሚሆነው ዋናውን ውል የሚመለከተው ሕግ ነው። ይህም ቢሆን ውል በመሆኑ በመደበኛው አሠራር የሕጎችን ግጭት የሚመለከቱት ደንቦች ተፈጻሚ ይሆኑበታል።[112]

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ክርክሩ የሚካሄድበትን ሁኔታ እንመልከት።

## ለ. ክርክሩ ለግልግል ሸንጎ በሚቀርብበት ጊዜ ፣

ዓለም አቀፍ ስምምነትን የሚመለከት ክርክር በሚነሳበት ጊዜ በግልግል ሸንጎው ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች አንዱ ክርክሩ መታየት የሚገባው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሳይሆን በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት ነው የሚል ሀሳብ ሊሠነዝር ይችላል። ለዚህም የሚያቀርባቸው ምክንያቶች ፣ የግልግል ስምምነቱም ሆነ ዋናው ውል የተደረጉት በውጭ ሀገርነው ፣ ወይም ውሉ የሚፈጸመው በሌላ ሀገርነው የሚሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ቀጥሉ የሚነሳው ጥያቄ ታድያ የዚህ ዓይነት ችግር ከፊቱ የተደቀነበት የግልግል ሸንጎ በምን ደንብ ሊመራ ይገባዋል የሚለው ነው። የመጀመሪያው መሪ ደንብ ተዋዋዮቹ የመረጡትን ሕግ መቀበል ነው። በሬኔ ዴቪድ አገላለጽ ፣

> "ዓለም አቀፍ የግልግል ሂደትን አስመልክቶ በተከራካሪ ወገኖች የተመረጠውን ፣ ወይም ሊመረጥ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ሕግ በተቻለ መጠን ተፈጻሚ የማድረግ አዝማሚያ እየተመረጠ መምጣቱ በግልጽ እየታየ ነው።"[113]

ተዋዋይ ወገኖች ተፈጻሚ የሚሆነውን ሕግ ያልመረጡ እንደሆነ ወይም ውጤታማ ምርጫ አላደረጉ እንደሆነ (ለምሳሌም ያህል በኢትዮጵያና ኢትአል በተባለ ድርጅት መሀከል በተደረገ ውል የኢትዮጵያና የግሪክ ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ የተባለውን መጥቀስ ይቻላል) በሥራ ላይ የሚውለው ዋናውን ውልና የግልግል ስምምነቱን የሚመለከተው "አግባብ ያለው" ሕግ ነው። ይህ አመለካከት በሚስተር ሴድለርም ጽሁፍ የተደገፈ ነው።[114] አሠራሩ ክርክሩ የሚታየው ውሉ በተደረገበት ሀገር ባለው ሕግ ነው "lex loci contractus"[115] ወይም ውሉ ተፈጻሚ በሚሆንበት ሀገር ሕግ ነው "lex loci solutions"[116] ከሚሉትና ከመሰል ደንቦች ይመረጣል። የእነዚህ የኋለኞቹ ደንቦች ዐቢይ ድክመት ደንቦቹ የግንኙነቱን አንዱን ገጽታ ብቻ የሚመለከቱ እመሆናቸው ላይ ነው። በሌላ በኩል ግን "አግባብ ያለው" ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው ደንብ የግልግል

---

112 የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን የሬኔ ዴቪድ ጽሁፍ ገጽ 217

113 ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ገጽ 220

114 ከላይ በተራ ቁጥር 106 ግርጌ ማስታወሻ የተጠቀሰው ሴድለር ጽሁፍ ገጽ 98

115 ከላይ የተጠቀሰው ጽሁፍ ገጽ 91

116 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 110 በተገለጸው ጽሁፍ ክፍል 3.2.1 በሐምሊንና ታልስከር ዲስትለሪ መካከል የነበረው ክስ

ሽንጎው የጉዳዩን ሁለንተናዊ ችግር እየመረመረ ለግልግሉ ስምምነት የበለጠ ቅርበት ያለውን ሀገር ሕግ ለቀረበለት ጉዳይ አወሳሰን እንዲጠቀምበት ይረዳዋል። ይህንን በሚያደርግበት ጊዜም ውሉ የተደረገበት ሥፍራ የት ነው ? ውሉ የሚፈጸምበት ሥፍራ የት ነው ? ግልግሉ የት ቦታ እንዲካሄድ ነው ስምምነት የተደረገው ? እና ተዋዋዮቹ የንግድ ሥራውን ያካሄዱት የት ቦታ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች እቁጥር ውስጥ ያስገባቸዋል።[117]

ተዋዋዮቹ የውጭ ሀገር ሕግ ተፈጻሚ እንዲሆን በመረጡበት ጊዜ ወይም የግልግል ሽንጎው እላይ በተገለጹት ደንቦች መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው የውጭ ሀገር ሕግ ነው የሚል ውሳኔ ላይ በደረሰ ጊዜ ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይህም የተመረጠውን የውጭ ሀገር ሕግ በመጠቀም ጉዳዩን ለመወሰን የሚቻለው እስከምን ደረጃ ድረስ ነው ? የሚለው ነው ። አሁን ያለውንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘውን አሠራር የተመለከትን እንደሆነ አለመግባባታቸውን የሚገዛውን ሕግ ተዋዋዮች ሊመርጡ እንደሚችሉ እንረዳለን።[118] በዚህ አሠራር ብዙ ግራ የሚያጋቡና የማያስተማምኑ ሁኔታዎችም ሊወገዱ ይችላሉ። ተዋዋዮቹ ችግሩ የሚታይበትን ሕግ አይምረጡ ብሎ መከልከል በገቢና ወጭ ንግድና በመዋዕለ ንዋይ ጥሪ ላይ የራሱን ደንታራ የሚያስቀምጥ በመሆኑ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚነካ ውጤት ሊያመጣ ይችላል። በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች ጉዳዩ የሚታይበትን ሕግ በመምረጥ ረገድ የሚኖራቸው መብት ማዕቀብ ሊጣልበት አይገባም። ዕገዳው ወይም ማዕቀቡ መደረግ ያለበት ተዋዋዮቹ በሚመርጡት የውጭ ሀገር ሕግ ወይም "አግባብ ያለው" ነው ተብሎ በገላጋዩ ሽንጎ በሚመረጠው የውጭ ሀገር ሕግ ይዘት ላይ ነው። በሀገሪቱ ውስጥ "የሕዝብን ፀጥታና ሰላም የሚያናጋ" ነው ወይም "ለመልካም ሥነ ምግባር ተፃራሪ" ነው የሚባል ሕግ ተቀባይነት እንደማያገኝ ግልፅ ነው።[119] እንደዚሁም አዛዥ ከሆኑ የሀገሪቱ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣም የውጭ ሀገርሕግም ተቀባይነት እንደማያገኝ ይታመናል። እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ባልተገኙበት ጊዜ ግን የግልግል ሽንጎው የውጭ ሀገር ሕግን ተፈጻሚ ቢያደርግ አግባብ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ተዋዋዮቹ ለጉዳዩ ተፈጻሚ የሚሆነውን ሕግ በስምምነታቸው ሳያመለክቱ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ በዓለም የንግድ ምክር ቤት የግልግል ደንቦች መሠረት ፥ ወይም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ ንግድን አስመልክቶ የሰየመው የግልግል ኮሚሲዮን ባወጣቸው ደንቦች መሠረት እንዲታይ ሲዋዋሉ ይስተዋላሉ። እነዚህ ደንቦች በሁሉም እቅጣጫ ተሟልተው የተዘጋጁ በመሆናቸው ወደ ዝርዝር ይዘታቸው መግባቱ አስፈላጊ አይደለም።[120] እዚህም ቢሆን ግን የውጭ ሀገር ደንቦችን በተመለከተ የሚጣሉት ማዕቀቦችና ገደቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ። (<u>ማስገንዘቢያ</u>:- ተዋዋዮቹ የዓለም የንግድ ምክር ቤትን ደንቦች የተቀበሉ ከሆነ ግልግሉ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢካሄድ የተሻለ መሆኑን የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አበክሮ ለማሳሰብ ይወዳል።

---

117 ከላይ በተራ ቁጥር 114 የገርጌ ማስታወሻ የሴድለር ጽሁፍ ገጽ 95 እና 98

118 ከላይ የገርጌ ማስታወሻ የተጠቀሰው ጽሁፍ ገጽ 84

119 የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ፥ የውጭ አገር የግልግል ዳኝነት አፈጻጸም ቁጥር 461 (1) (ሠ) ይመልከቱ።

120 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 109 በተጠቀሰው ጽሁፍ ገጽ 581

የተመረጠው የተባበሩት መንግሥታት የግልግል ኮሚሲዮን ያወጣው ደንብ ሲሆን ደግሞ ገላጋዩን የሚሰይመው አካል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ቢሆን ይበጃል።)

ሐ. <u>ክርክሩ ለፍርድ ቤቶች በሚቀርብበት ጊዜ ፣</u>

ግልግልን የሚመለከት ክርክር በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊቀርብ የሚችልበት አንዱ አጋጣሚ አንደኛው ወገን ገላጋይ እንዲሰየምለት ለፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ ሌላኛው ተዋዋይ ክርክሩን በውጭ ሀገር ሕጎች በመመሥረት የግልግል ስምምነት የለም ብሎ ሲቃወመው ነው። በዚህ ወቅት ፍርድ ቤቱ እላይ የተገለጹትን የሕጎችን ግጭት የሚመለከቱትን ደንቦች ተፈጻሚ ከማድረግ ውጭ የተለየ ምርጫ የለውም የሚል አመለካከት በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ዘንድ አለ። (እዚህ ያለው መጠነኛ ልዩነት የግልግል ሸንጎው ገና ያልተቋቋመ መሆኑ ብቻ ነው።) ከዚህ በመቀጠል በቀድምያ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆነው የትኛው ሕግ እንደሆነ ይበይናል። ከዝያም ተፈጻሚ ነው የተባለውን ሕግ መለክያ በማድረግ የግልግል ስምምነት መኖር አለመኖሩን ፣ ወይም አለ የተባለው የግልግል ስምምነት በሚፀና አኳኋን የተደረገ መሆን አለመሆኑን ይወስናል።

ሌላው አጋጣሚ ደግሞ አንድ ከሳሽ ክሱን በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በሚያቀርብበት ጊዜ ፣ ተከሳሹ በበኩሉ በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት የተደረገ የግልግል ስምምነት አለና ጉዳዩ በፍርድ ቤት አይታይም ብሎ በተቃወመ ጊዜ ፣ ከሳሹ ደግሞ ስምምነቱን ሳይክድ ይህ ስምምነት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሕገ ወጥ ነው ብሎ በሚከራከርበት ጊዜ ፣ የሚነሳው ውዝግብ ነው። ይህን የመሰለ ክርክር ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ የተባለውን የውጭ ሀገር ሕግ በዝርዝር መመልከትና ስምምነቱ ለመልካም ሥነ ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑን ፣ ፀንተው ያሉ አዛዥ የሕግ ደንቦችን የሚቃረን መሆን አለመሆኑን መመርመር ይገባዋል። ለምሳሌ የተባለው የውጭ ሀገር ሕግ ገላጋይ ጉዳዩን በሕግ ብቻ ሳይሆን በአስተያየትና በርትዕም ጭምር አይቶ እንዲወስን የሚፈቅድ ከሆነ ይህ ሕግ አዛዥ ከሆነ የኢትዮጵያ ሕግ ጋር የሚፃረር በመሆኑ ውጤት አይኖረውም።[121]

## <u>ክፍል አምስት</u>

### <u>የግልግል ዳኝነት የንግድ አለመግባባቶችን ለመፍታት</u><br><u>የተሻለ ዘዴ ስለመሆኑ ፣</u>

በንግድ ሕብረተሰብ አባላት መሀል አለመግባባቶች በሚነሱበት ጊዜ እነዚህ አለመግባባቶች መፍትሄ የሚያገኙባቸው አያሌ ብልሀቶች አሉ። የሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት ሳያስፈልጋቸው ራሳቸው ተዋዋዮቹ በድርድርና ከእኔም ካንተም ይቅር ተባብለው ለችግሩ መላ ማበጀት ይችላሉ። ነገር ግን በሁለቱ ወገኖች መሀከል ያለው ግንኙነት የሻከረ ከሆነና አለመተማመንም ከተከሰተ ይህኛው መንገድ እንደምንገምተው ቀላል ላይሆን ይችላል። ችግሩ እየጎላ ከመጣ የሦስተኛ ወገን በጉዳዩ ጣልቃ መግባት

121 ቁጥር 3325 (1) ፍ.ሕ.

አስፈላጊ ይሆናል። በመቀጠልም አስማሚ በጋራ ሊመርጡ ይችላሉ። እዚህም ቢሆን ተዋዋዮቹ በአስማሚው ውሳኔ ለመገዛት በጽሁፍ ማረጋገጫ ካልሠጡ በስተቀር ይህ አካል በሚሠጠው የውሳኔ ሀሳብ ገራ ቀኙ አይገደዱበትም።[122] እሱ የሚሠጠውን የውሳኔ ሀሳብ በአስገዳጅነት እንዲከተሉ ማድረግ ራሱ የአስማሚውን ከፍተኛ ችሎታ የሚጠይቅ ነው።

ሌላው አማራጭ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ ነው። ነገር ግን አሁን ያለውን የኢትዮጵያ ሁኔታ ስንመለከት የዳኞች ቁጥር ከሚቀርቡላቸው ጉዳዮች ብዛት ጋር የማይጣጣም መሆኑ ገሀድ ኒው። በ1982 ዓ.ም ብቻ 95,000 የፍትሐ ብሄርና 115,000 የወንጀል ጉዳዮች ለአውራጃና ለከፍተኛው ፍርድ ቤቶች ቀርበው ነበር።[123] በቀረበው ጉዳይ ላይ ፍርድ ለማግኘት ረዥም ጊዜ ያስፈልጋል። ሥርዓቱ ራሱ ሦስት የይግባኝ ደረጃዎች አሉት። የዳኞች ደመወዝ የሚፈለገውን ያህል ከፍተኛ አይደለም። የደመወዝ ጭማሪ ተደርጎ አያውቅም። የኑሮ ውድነቱ እየናረ ነው። ከዚህ አንጻርቢታይ የጉቦኝነት መስፋፋት ሊያስገርመን አይገባም። ከዚህም ሌላ ዳኞች በልዩ ሕጎች ሥልጠና የሌላቸው በመሆኑ ውስብስብ የሆኑ የንግድ ግንኙነትን የሚመለከቱ ደንቦችንና አሠራሮችን በቅጡ ላይረዱ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ከአንድ ችሎት ወደ ሌላ ችሎት እንዲዘዋወሩ የሚደረግ በመሆኑ በራሳቸው ጥረትም ይህን ልዩ ሥልጠና የማግኘት ዕድሉ የላቸውም።

እንግዲህ ባለነገር ለሆነ ነጋዴ የሚቀረው አማራጭ ጉዳዩን በገልገል መጨረስ ነው። ይህም አሠራር ቢሆን ፍጹም ነው የሚል መልዕክት የማስተላለፍ ፍላጎት የለኝም። እሱም የራሱ ችግሮች አሉት። በመስኩ የተካኑና ሕጉንም ጠለቅ ብለው የሚያውቁ ገላጋዮችን ማግኘት ቀላል አይደለም። ገላጋዮች በሚሰየሙበት ጊዜ ፥ በሚሠጡት ውሳኔ ላይ ይግባኝ በሚባልበት ጊዜ ፥ የሚሠጡት ውሳኔ በሚፈጸምበት ጊዜ ሁሉ የዳኞችን እርዳታና ድጋፍ ማግኘቱ የግድ ይሆናል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ የገልገልን ሂደት እና አጠቃቀም የሚያበረታቱና የሚያጠናክሩ በአግባቡ የተዋቀሩ ተቋሞች የሌሉ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል። እነዚህ ችግሮች ቢኖሩም ክርክር ከመነሳቱ በፊት በጥንቃቄ የተዘጋጀ የገልገል ስምምነት ካለ የገልገል አሠራር አለመግባባቶችን ለመፍታት የተሻለ ዘዴ ሆኖ ማገልገል ይችላል። በተለይም ክርክሩ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ካለውና እንደ የነዳጅ ማውጣት ሥራን ፥ የታላላቅ ፕሮጀክቶች ተቋራጭነት ሥራን ፥ የሚመለከት ወይም እጅግ በርካታ ገንዘብን የሚያካትት ፥ በሚሆንበት ጊዜ የገልገል ዳኝነት አማራጭ መሆኑ ቀርቶ ችግሩን የመቁረጫ ብቸኛው መንገድ ይሆናል።

---

122 ቁጥር 3332 (1) ፍ.ሕ.

123 ከፍትሕ ሚኒስቴር እስታቲስቲክስ ክፍል የተገኘ መረጃ።